# የተማሪ እና ሠራተኛ፣ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ የመጠቀሚያ ፖሊሲ

## I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

የዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS)፣ ለተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ የኢንተርኔት፣ የመረጃ ስብስብ (data) እና የኔትወርክ ዘዴዎችን (DCPS network) እንዲያገኙ ያደርጋል። DCPS በተጨማሪም ለተማሪዎች እና ሠራተኞች - የኮምፒውተሮች፣ የታብሌቶች፣ ዲቫይሶች፣ እና ሌሎች የቴክኖሎጂ ውጤቶችን - እንደ ፕሪንተሮች (printers) የመሰሰሉትን (የDCPS ዲቫይሶች ወይም ቴክኖሎጂ)፤ ያቀርባል። የDCPS አውታረ መረብ (network) እና የDCPS ቴክኖሎጂ፣ ለማቀድ፣ የትምህርት አሰጣጥ፣ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲባል ለሠራተኛ የሚሰጡ እና ለተማሪዎች ደግሞ ለትምህርታዊ ሂደቶች፣ ምርምር፣ እና የስራ እድገት ማግኛነት ሆነው ያገለግላሉ። ይህ ፖሊሲ ዒላማ የሚያደርገው:

- ለDCPS ኔትወርክ እና ለDCPS ቴክኖሎጂ፣ መሠረታዊ ደረጃውን የጠበቀ ተቀባይነት-ያለው አጠቃቀምን መመስረት፤
- አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (artificial intelligence)ን በመጠቀም-ዙሪያ፣ ኃላፊነትን በመውሰድ የሚጠበቁባቸውን-ነገሮች ማስቀመጥ፤
- የDCPS ኔትወርክ እና የDCPS ቴክኖሎጂን ፈቃድ-የሌላቸው እና ሕጋዊ-ያልሆኑ ጥቅሞች ላይ እንዳይውል መከላከል፣ እና
- ከ'Children's Internet Protection Act of 2000 (CIPA)'፣ ከ'Children's Online Privacy Protection Act (COPPA)'፣ ከ'Protecting Students Digital Privacy Act'፣ እና ሌሎች ከዚህ ጋር የሚሄዱ ሕጎች፣ ደንቦች፣ ፖሊሲዎች እና ማካሄጃዎች ጋር - አብሮ ከሚሄዱት-ጋር ሁሉ፣ ተገዢ-መሆን፤

ይህ ፖሊሲ፤ ለሁሉን የDCPS ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ ጎብኚ-እንግዶች፣ እና ሌሎች የDCPS ኔትወርክን ወይም ዲቫይሶችን የሚጠቀሙ ሁሉ የሚመለከት እና ከዚህ-ቀደም የነበረውን የDCPS፣ የተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ መጠቀሚያ ፖሊሲ (DCPS Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy (2021)ን የሚሽር-ነው።

## II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ (AUTHORITY AND APPLICABLE LAW)[1]

| ምንጭ | ጥቅስ (Citation) |
|---|---|
| የፌደራል ሕግ | - የልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ድንጋጌ (Children's Internet Protection Act (CIPA)፣ በኮድ-የተለየው/codified በ47 U.S.C. § 254(h)(5)<br>- የልጆች የኦንላይን የየግል-ጥበቃ መከላከያ ድንጋጌ - 1998 (Children's Online Privacy Protection Act of 1998 (COPPA)፤ በኮድ-የተለየው/codified በ15 U.S.C. § 6501 *et seq.*<br>- የአጎራባች የልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ድንጋጌ (Neighborhood Children's Internet Protection Act)፤ በኮድ-የተለየው/codified በ47 U.S.C. § 254(l) |
| የፌደራል ደንቦች | - የልጆች የኦንላይን የየግል-ጥበቃ መከላከያ ደንብ (Children's Online Privacy Protection Rule)፣ 16 C.F.R. Part 312 |

[1] በዚህ ፖሊሲ ውስጥ ምንም-ነገር፣ የፌደራል፣ ስቴት፣ ወይም የአካባቢው (local) ሕግን የሚተካ አይደለም።

| | |
|---|---|
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ | - የተማሪዎችን የዲጂታል የግል-ማንነትን መጠበቂያ ድንጋጌ (Protecting Students Digital Privacy Act of 2016)፣ የዲሲ ሕግ/D.C. Law 21-218, በኮድ-የተለየው/codified በD.C. Official Code 38-831.01 *et seq*. |
| የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች | - 5-B DCMR § 2500 *et seq*. – የተማሪ ስነ-ስርዓት/Student Discipline<br>- 6-B DCMR § 1610 – የሠራተኛ የስነ-ስርዓት ማረቢያ (Employee Progressive Discipline) |

## III. ቁልፍ-የሆኑ አባባሎች እና ትርጉሞች

**አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (Artificial Intelligence (AI)** ማለት፤ የኮምፒውተር ሣይንስ አንዱ-ቅንጫፍ ሆኖ፣ በኮምፒውተሮች ውስጥ በላቀ-የአዕምሮ-ብስለት ባህሪያቶች ጎን-ለጎን ሆኖ በአንድ-ላይ የሚሠራ-ነው።

**የDCPS ኔትወርክ** ለሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በDCPS የተሠጡ፤ የኢንተርኔት፣ የመረጃ ስብስብ (data)፣ እና የኔትወርክ ዘዴዎች

**የDCPS ሠራተኛ** ሁሉም የDCPS ተቀጣሪዎች (በሙሉ ወይም የግማሽ ሰዓት)፣ በኮንትራት፣ ድርጅቶች፣ ወኪሎች፣ በጎ-ፈቃደኞች፣ ወይም ሌላ ማንኛውም DCPSን በመወከል የሚሰራ ግለሰብ፣ የDCPS ኔትወርክ ወይም የDCPS ቴክኖሎጂን ለመጠቀም የሚችል-ማለት ነው።

**የDCPS ቴክኖሎጂ** በDCPS - ለተማሪዎች እና ሠራተኞች የተሠጡ፤ ኮምፒውተሮች፣ ታብሌቶች፣ ዲቫይሶች፣ እና ሌሎች ቴክኖሎጂዎች - ማለት ነው።

**መባረር (Expulsion)** ተማሪውን ከሚማርበት ትምህርት ቤት በስነ-ስርዓት ችግሮች ምክንያት፣ ከአካባቢ የትምህርት ድርጅት ፖሊስ (local education agency policy)ን በተከተለ-ሁኔታ፣ ከቀሪው የትምህርት ዓመት ወይም ከዚያ በላይ ማስወጣት - ማለት ነው።

**የግል መረጃ**: ለብቻው ወይም ከሌላ ጠቃሚ የመረጃ ስብስብ (data) ጋር በአንድነት፣ መረጃዎችን በመጠቀም እንደ የግል መረጃ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል። የግል መረጃ/Personal information፣ የሚከተሉትን፤ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ ሙሉ ስም፣ የቤት ወይም ሌላ የመኖሪያ አድራሻ፣ እንደኦንላይን የመገኛ መረጃነት የሚያገለግል የስክሪን (screen) ስም ወይም የመጠቀሚያ ስም (user name)፣ እና የግለሰቦችን ምስል ወይም ድምፅ የያዙ የፎተግራፍ፣ የድምፅ፣ ወይም የቪዲዮ ፋይሎችን - ያካትታል።

**የስነ-ስርዓት እርማት-ማድረጊያ እርምጃ (Progressive Discipline)** የ ማለት፣ የሠራተኞች የስነ-ስርዓት መቅጫ ዘዴ ሲሆን፣ በሠራተኞች የሥራ ክንውን እና/ወይም የጠባይ ችግሮች ላይ፣ የበላይ የአፈጻጸም ምላሽ የሚሰጥ-ማለት ነው። የDCPS የስነ-ስርዓት እርማት-ማድረጊያ እርምጃ (progressive discipline) የአሰራር-ደረጃዎች ሆነው የተካተቱት፤ በቃል የሚደረግ ምክርን፣ ማስጠንቀቂያ፣ ትግሣጽ፣ እና የቅጣት-እርምጃ (adverse action)ን - ይጨምራል።

**እገዳ**: ተማሪው፣ የስነ ስርዓት ቅጣትን በተከተለ ምክንያት፣ ከትምህርት ቤት መደበኛ የክፍለ ጊዜ ሰሌዳ እንዲወጣ ተደርጎ፣ ተማሪው በትምህርት ቤት ሠራተኛ ተቆጣጣሪዎች ጥበቃ ስር ሆኖ በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዲቆይ ሲደረግ፤ ወይም ተማሪው በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እንዳይገኝ በማድረግ በጊዜያዊነት ማገድ።

## IV. መስፈርቶች

### A. አጠቃላይ (General)

DCPS፣ የDCPS ኔትወርክን እና የDCPS ቴክኖሎጂን ለሠራተኞችና ተማሪዎች ጥቅም ላይ እንዲውል ያቀርባል፤ ፈቃድም ይሰጣል። DCPS የቴክኖሎጂ የመገኛ-ምንጮች (technology resources)ን-ለመጠቀም ፈቃድ-በመስጠቱ እና በማቅረቡ፤ በDCPS በተሰጡት ዘዴዎች - ላይ፣ የቴክኖሎጂ እና የቁሳቁሶች/materials ባለቤትነትን ወይም ቁጥጥርን አይለቅም። ከዚህ በታች በተገለጸው አኳሃን ካልሆነ በስተቀር፣ በDCPS ኔትወርክ ወይም በDCPS የመገናኛ ዘዴዎች ላይ በተቀመጡት ወይም በተሰራጩት መረጃዎች ላይ ከግላዊነት ጋር በተያያዘ ሁኔታ በማስተማመኛነት መያዝ የማይቻል መሆኑን እና፤ በDCPS ቴክኖሎጂ እና በDCPS ኔትወርክ አካውንቶቹ እና በመገናኛነት በሚጠቀምባቸው በሁሉም የDCPS ኔትወርክ ላይ የተቀመጡ ፋይሎቹን፤ የማግኘት፣ የመገምገም፣ የማባዛት፣ የማስቀመጥ ወይም የማጥፋት መብት አለው። በDCPS ኮምፒውተሮች ውስጥ የተቀመጡ ወይም የDCPSን የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም የተሰራጩ የኤሌክትሮኒክ መልዕክቶችንና ፋይሎችን፣ ልክ እንደሌላ የትምህርት ቤቱ ንብረቶች ሊታዩ ይችላሉ። የDCPS ሠራተኞች፣ ምርመራ-ለማድረግ፣ ህጋዊ መስፈርቶችን ለማክበር፣ የስርዓቱን ታማኝነት ለመጠበቅ፣ እና አስፈላጊ-ሆኖ ከተገኘ - የቴክኖሎጂ እና የኔትወርክ ተጠቃሚዎች - በኃላፊነት እና ከዚህ-ፖሊሲ ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ በሚሄድ ሁኔታ ማከናወናቸው - ለማረጋገጥ፤ በፋይሎች እና በመልዕክቶች-ላይ ምልከታ ሊያደርጉ ይችላሉ። በDCPS - ለተማሪዎች ወይም ሠራተኞች የተፈጠሩት-ሁሉን አካንውቶች፤ በDCPS ቁጥጥር-ሊደረግባቸው ይችላል።

1. ተማሪዎች

DCPS፣ የዚህን-ፖሊሲ ማስታወቂያ - በዓመታዊ የምዝገባ ሂደት አማካኝነት-ያቀርባል፣ እና ሁሉም ወላጆች እና አዋቂ-ተማሪዎች፣ እንደደረሳቸው እንዲያሳውቁ ይጠየቃሉ። የተማሪ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-በሆነ ሁኔታ የመጠቀም (Student Technology and Network Responsible Use) ስምምነት (የተማሪው፣ ኃላፊነት-በተመላው ሁኔታ የመጠቀም ስምምነት)ን - አባሪዎች (Appendices)ን እና በDCPS ድህረ-ገጽ ላይ ያለውን አካትቶ፤ ተማሪዎች እና ወላጆች እንዲፈርሙ ሊጠየቁ ይችላሉ። የተማሪ በኃላፊነት-የመጠቀም ስምምነት፤ ተማሪዎች፣ የDCPS ቴክኖሎጂን ወይም የDCPS ኔትወርክን በሚያገኙ ጊዜ፣ የመጠቀሚያ ኃላፊነትንና የተከለከሉ እንቅስቃሴዎችን ዘርዝሯል። ትምህርት ቤቶች፣ የቴክኖሎጂ መግቢያ/መውጫ ሂደቶችን በዝርዝር የሚከተሉ፣ የተለየ ከቴክኖሎጂ ጋር ግንኙነት ያለው የትምህርት ቤት ሠራተኛን የስራ መደብ የሚጠይቅ፣ እና የትምህርት ቤቱ የተለየ ደንቦችን የሚጠቀም፣ የራሱ የሆነ የትምህርት ቤት መለያ የሆነ ስምምነቶችን ተማሪዎች እና ወላጆች እንዲፈርሙ ይጠይቅ ይሆናል።

DCPS ለተማሪዎች፣ ከዓመታዊ የዲጂታል ጥሩ-ዜጋ መሆን (digital citizenship)ን እና የኦንላይን ደህንነት-ጥበቃ ትምህርቶችን ያቀርባል። በዲቫይስ-አጠቃቀም እና እንክብካቤ ሞጁል/module ላይ ያለውን-ጨምሮ፣ ተማሪዎች በዲጂታል ጥሩ-ዜጋ መሆን (Digital Citizenship) እና ማንበብና-መጻፍ የተማሪ ማዕከል (Literacy Student Hub)[2] ውስጥ ኮርሶችን እንዲያጠናቅቁ ይጠበቅባቸዋል፤ እና ለተማሪው፣ የDCPS ዲቫይስ ወይም አካውንት ከመሰጠቱ-በፊት፣ ኮርሱን ማጠናቀቅ ሊያስፈልግ-ይችላል።

እነዚህን ደንቦች ለመከተል አለመቻል፣ በDCPS የተማሪ የስነ-ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎች ስር - 'ደህንነቱ-የተጠበቀ እና አዎንታዊነት ያላቸው ተማሪዎች ፖሊሲ (Safe and Positive Students Policy)ን[3] ጨምሮ፣ ምላሽ-የሚሰጥባቸው እና፣ ተማሪዎቹ - በአማራጭ-መንገዶች አማካኝነት የክፍል-ስራዎችን ለማጠናቀቅ እና ሁሉንም አስፈላጊ የሆኑትን - የልዩ ትምህርት (special education) እና የእንግሊዘኛ ቋንቋ ለሚማሩ አገልግሎቶች ውስጥ ለመሣተፍ፣ ለተራዘመ-

---

[2] በhttps://dcps.instructure.com/enroll/Y8Y7KY ላይ የሚገኝ።

[3] በhttps://dcps.dc.gov/page/dcps-policies ላይ የሚገኝ።

ጊዜ የDCPS ኔትወርክን ወይም የDCPS ቴክኖሎጂን ማግኘት-ሳይችሉ ሊያሳጣቸው ይችላል። በአንዳንድ ሁኔታዎች፤ መጥፎ ባህሪይ፣ የወንጀለኛ ጥሰትን ሊፈጥሩም ይችሉ ይሆናል።

2. ሠራተኛ (Staf)

DCPS - የዚህን-ፖሊሲ ማሳሰቢያ፣ ለአዳዲስ ሠራተኞች በቅጥር-ሂደትጊዘ የሚያቀርብ፤ እና የሠራተኞች ቴክኖሎጂን በኃላፊነት-የመጠቀም ስምምነት/Staff Technology Responsible Use Agreement (የሠራተኞች የኃላፊነት መጠቀም ስምምነት) በአባሪዎች/Appendices ውስጥ የተካተተውን - እንደ ተጨማሪ እና ቀጣይ ማጣቀሻ-ሆኖ፣ በDCPS ድህረ-ገጽ ላይ ይገኛል። የDCPS ዲቫይስ የተሰጣቸው ሠራተኞች - ከመቀበላቸው-በፊት ወይም በሚቀበሉበት ጊዜ - የሠራተኛ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት-የመጠቀም ስምምነት - እውቅና-መስጫ ቅጽ (Staff Technology Responsible Use Agreement Acknowledgement Form) ላይ እንዲፈርሙ ወይም እንደገና-እንዲፈርሙ ሊጠየቁ ይችላሉ።

የዲሲ መንግስት (The DC Government)፣ የዲሲ ዋናው የቴክኖሎጂ ቢሮ ባለስልጣን (DC Office of the Chief Technology Officer (OCTO) እና/ወይም DCPS፤ ከሳይበርሴኩሪቲ/cybersecurity ወይም ተያያዥ-የሆኑ ርዕሶች ጋር የሚሰጡ - የተቀጣሪ-ሠራተኞች ስልጠናዎችን፣ ሠራተኞች እንዲወስዱ ይጠይቅ ይሆናል። ጊዜውን-በጠበቀ ሁኔታ፣ እነዚያን ስልጠናዎች ለማጠናቀቅ-አለመቻል ወይም ይህንን ፖሊሲ መከተል ያልቻሉ ሰራተኞች፤ ወደ የስነ-ስርዓት እርማት-ማድረጊያ እርምጃ (progressive discipline) ሊያጋልጣቸው-ይችላል።

### B. ኔትወርክ፣ ኢሜል እና አፕሊኬሽኖች

1. ኔትወርክ/አውታረ መረብ (Network)

የDCPS አውታረ መረብ (network) እና የDCPS ቴክኖሎጂ፣ ለማቀድ፣ የትምህርት አሰጣጥ፣ እና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲባል ለሠራተኛ የሚሰጡ እና ለተማሪዎች ደግሞ ለትምህርታዊ ሂደቶች፣ ምርምር፣ እና የስራ እድገት ማግኛነት ሆነው ያገለግላሉ። በDCPS ኔትወርክ አማካኝነት ለሠራተኞች እና ተማሪዎች ውስጣዊ የማግኘት መብትን በመስጠት፣ ወደ የDCPS መረጃዎችና የመረጃ ምንጮች፣ በDCPS የተፈቀዱ ማመልከቻዎችን፣ እና ውጫዊ የማግኘት መብቶችን በኢንተርኔት ያስገኛል። የDCPS ኔትወርክን ማግኘት፣ ተማሪውን በብቸኝነት - በትምህርት፣ በምርምር፣ እና በሥራ-መስክ ዕድገት ለመደገፍ ሲባል፤ ኢንተርኔትን ጨምሮ - ለተማሪዎች ይሰጣል። የDCPS ኔትወርክን መጠቀም፣ ልዩ-የሆነ ዕድል ነው። ማንኛውም የዚህ ፖሊሲ ክፍል ወይም ተዛማጅ የሆኑ ፖሊሲዎችን የሚጥሱ ሠራተኞችና ተማሪዎች፣ ይህንን የDCPS ኔትወርክ የመጠቀም ልዩ እድል እንዲሰረዝባቸው ሊያደርጋቸውና የስነ ስርዓት መቅጫ እርምጃንም ሊያስከትል ይችላል።

የኔትወርክ ማግኘት እና ባንድዊድዝ (bandwidth)፤ ለትምህርት ቤቶች የሚሰጠው፣ ለቀለም-ትምህርት እና ማከናወኛ አገልግሎቶችን ማካሄጃ ነው። DCPS የኔትውርክ ባንድዊድዝን ቅድሚያ የመስጠትና የተወሰኑ በስርዓተ ትምህርቱና ክንውኖቹ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ የኔትወርክ እንቅስቃሴዎችን የመገደብ መብቱ የተጠበቀ ነው። የኔትወርኩ ተጠቃሚዎች፣ አግባብነት የሌላቸው ወይም ሕገወጥ ይዘት ያላቸውን ነገሮችን፣ የሚከተሉትን፤ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ፣ እንደ የወሲብ ክንውን (pornographic)፣ ፀያፍ፣ ሕገወጥ፣ ወይም ዓመጽን አነሳሽ የሆኑ ነገሮችን በDCPS ኔትወርክ እንዳይጠቀሙ ይከለክላል።

DCPS በኔትወርክ አገልግሎቱ ላይ የሚሰጠው ተግባራት ወይም ጥራት ሁሉ ከማንኛውም ስህተት ወይም ብልሽት ነፃ መሆኑን ሙሉ ለሙሉ ዋስትና አይሰጥም። ለማንኛውም አቤቱታዎች፣ የጠፉ ነገሮች፣ ጉዳቶች፣ ክፍያዎች፣ ወይም ኔትወርኩን ወይም አካውንቶቹን በመጠቀም የሚመጡ ሌሎች ግዴታዎችን ላይ፣ DCPS ኃላፊነት አይወስድም። በማንኛውም የኔትወርክ አጠቃቀም የሚመጣ የክፍያ መጠየቂያ፣ የግለሰቡ የግል ሸክም ይሆናል። ከDCPS የተሰጠ ይዘት ያለው መረጃ ካልሆነ በስተቀረ፤ የመረጃ ዘዴውን በመጠቀም የሚገኙ መረጃዎችን ትክክለኛነት ወይም ጥራት-ላይ፣

DCPS ኃላፊነት አይወስድም። በኔትወርኩ ወይም ከኢንተርኔት ላይ የሚገኙ በDCPS ያልተሰጡ ማንኛውም መረጃዎች፤ የፀሐፊውን የግል አመለካከትን የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን መረዳት እና የDCPS፣ የኮሎምብያ ዲስትሪክት መንግስት፣ የተባባሪዎቻቸው፣ ወይም የተቀጣሪ-ሠራተኞቹ - እንዳልሆኑ ግንዛቤ-ውስጥ አስገቡ።

2. ማጣራቶች እና ክትትል

በ'ልጆች የኢንተርኔት ጥበቃ ድንጋጌ (Children's Internet Protection Act (CIPA) ስር በሚጠየቀው መሠረት፤ DCPS ተማሪዎችን መጠበቅ እና ስለኦንላይን ስጋቶች፣ አግባብነት የሌላቸው ይዘቶችን መዝጋት፣ እና በትምህርት ቤት ኔትውርኮች[4] ላይ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ (minors)ን አጠቃቀማቸው ላይ ክትትል በማድረግ መጠበቅ-አለበት።

ለአቅመ አዳም ላልደረሱ ፀያፍ፣ የወሲብ ክንውን (pornographic)፣ ወይም ጉዳይ የሚያስከትሉ የምስል ማሳያዎችን ከኢንተርነት መገኛዎች ለማገድ ወይም ለማጣራት፣ DCPS የቴክኖሎጂ መከላከያዎችን ይጠቀማል። ከዚህ-በታች፣ በክፍል/Section IV.G ከተገለጸው በስተቀር፣ DCPS የተማሪዎችን የኦንላይን እንቅስቃሴዎች እና የሚያዩዋቸውን ነገሮች በመቆጣጠርና በመከታተል፣ እና ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን ወይም ፋይሎችን፤ ማግኘት፣ ምልከታ-ማድረግ፣ በቅጂ ማባዛት፣ እና ማስቀመጥ ወይም ማንኛውንም የኤሌክትሮኒክስ መረጃዎችን ማጥፋት/delete ማድረግ፤ እንዲሁም አስፈላጊነቱ-ከታመነ፣ ለሌሎችም የማሳወቅ መብቱ የተጠበቀ ነው። የ'ተማሪዎችን የዲጂታል ግላዊነት ድንጋጌን መጠበቅ (Protecting Students Digital Privacy Act' (ከታች ክፍል/Section IV.G ተመልከቱ) በተመለከተው ካልሆነ በስተቀር፣ የDCPS ንብረትን፣ የDCPS የኮምፒውተር ኔትወርክን ወይም ኢንተርኔትን፣ ፋይሎችን፣ ወይም ኢሜልን በዚሁ ኔትወርክ ውስጥ ሆነው ሲጠቀሙ፤ ተማሪዎችን ግላዊነትን-የሚጠብቅ (privacy ለመጠበቅ) ምንም-የሚጠብቁት ነገር አይኖራቸውም።

እንዲሁም DCPS የደህንነት የአመራር ዘዴን ተጠቅሞ፣ በኦንላይን የተማሪ የፋይል ማከማቻ፣ ገቢና ወጪ የDCPS ኢሜልን፣ የDCPS ኢሜል አባሪዎችን (attachments)፣ እና ወደ ድህረ-ገጽ ማገናኛ ሊንኮችን ይዘታቸውን ጥናት እና ምርመራ ያደርጋል። ይህ ዘዴ ጎጂነት አላቸው ተብሎ የሚታሰቡ ይዘቶችን እና ምስሎችን የሚያግድ እና የአስቸኳይ-ጊዜ ሁኔታዎች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ለራስ ወይም ለሌሎች እንደ የማስፈራሪያ/threat ወይም ጥቃት/violence - ማስጠንቀቂያ - ለDCPS ሠራተኛ ማስታወቂያ-ያደርጋል።

3. አፕሊኬሽኖች (Applications)

የልጆች በኦንላይን ግላዊነት ጥበቃ ድንጋጌ (The Children's Online Privacy Protection Act (COPPA)፣ የድህረ-ገጹ ተቆጣጣሪዎች ወይም ከ13 ዓመት በታች የሆኑ ልጆች የኦንላይን አገልግሎቶች የተመሩ፣ እና ከ13 ዓመት በታች ከሆኑ ልጆች የግል መረጃዎችን በኦንላይን የሚሰበሰቡ ትክክለኛ እውቀት ያላቸው የሌሎች ድህረ-ገጾች ተቆጣጣሪዎች፣ መረጃውን ከመሰብሰባቸው፣ ከመጠቀማቸው ወይም የልጆቹን[5] የግል መረጃዎች አሳልፈው ከመስጠታቸው በፊት፣ የወላጅ ፈቃድ የተሰጠበትን ስምምነት ማግኘት ያስፈልጋቸዋል።

ለDCPS መገልገያና ጥቅም እንዲውል እና ለሌላ ምንም ዓይነት የንግድ ስራ ላይ የማይውል፣ የግል መረጃዎችን ከድህረ-ገጽ ወይም ከኦንላይን ለመሰብሰብ ኮንትራክት ሲገባ፣ ከDCPS የማግኛ የፈቃድ ስምምነት ማግኘት የሚችልና በቀጥታ

[4] 47 U.S.C. 254(h)(5)(B).

[5] 16 C.F.R. Part 312.5 ተመልከቱ። ይህ መስፈርት፣ ወላጅ ከዚህ-ቀደም ፍቃድ በሰጡባቸው ስብስቦች፣ አጠቃቀሞች ወይም ይፋ-የማድረግ ልማዶች ላይ በሚገኝ-ማንኛውም የቁሳቁስ/material ለውጥ ላይም በስራ-ላይ ይውላል። ኦፕሬተሮች (Operators) በተጨማሪም፣ የልጁን የግል መረጃ (personal information)ን ለሶስተኛ ወገኖች ይፋ ለማድረግ ሳይስማሙ፣ የልጁን የግል መረጃ ለመሰብሰብ እና ለመጠቀም - ለወላጆች ፍቃድ የመስጠት አማራጭን-መስጠት አለባቸው።

የወላጆችን[6] የፈቃድ ስምምነት ማግኘት አያስፈልገውም። ሁሉም የCOPPA-ተገዢ የሆኑ ድህረ-ገጾች እና የኦንላይን አገልግሎቶች፣ DCPS ኮንትራት የወሰደባቸው እና/ወይም ከ13 ዓመት-በታች የሆኑ ተማሪዎች ማግኘት እንዲችሏቸው የተደረጉ፣ የእያንዳንዱ አቀናባሪ የሆነን የግል ፖሊሲ ሊንክን ጨምሮ፣ እና ወላጆች ካልፈለጉ ለመውጣት (opt out) ምን ዓይነት ሂደትን መከተል እንደሚገባቸው የሚያሳይ፣ የDCPS የኤሌክትሮኒክ የዕቃ ዝርዝር (inventory) በሆነው የDCPS ድህረ-ገጽ ላይ የቀረበውን፣ የስምምነት ማስታወቂያ ለወላጆች ያቀርባል። ለ'non-COPPA' ተገዢ ያልሆኑ ድህረ-ገጾችን እና አገልግሎቶችን፣ ወይም ማንኛውም በ'COPPA'-ተገዢ ድህረ-ገጾችን እና አገልግሎቶችን ለመጠቀም፣ የግል-መረጃ እንዲሰበሰብ - ቤተሰቦች ፈቃድ-ባልሰጡበት ሁኔታ፤ ከ13 ዓመት በታች ለሆኑ ተማሪዎች - የDCPS ሠራተኞች ለተማሪዎች መፍቀድ አይችሉም።

4. የማግኘት ፈቃድን መቆጣጠር (Access Control)

DCPS የደህንነት ጥበቃ ያለው የማግኘት ፈቃድ ቁጥጥር እርምጃዎችን የሚወስደው፣ ሁሉም ተገቢ የሆነው ኔትወርክ እና ቴክኖሎጂን የማግኘት ፈቃድን ለሁሉም ተጠቃሚዎች ማግኘት-እንዲችሉ እና ፈቃድ-የሌላቸው እና ስጋት ፈጣሪ ናቸው ተብለው የሚገመቱትን ቆልፎ ለማስወጣት (lock out) ነው። DCPS፣ የተጠቃሚዎችን የማግኘት ፈቃድን፣ እንደ DCPS ኔትወርክ፣ የDCPS ኢሜል አካውንቶች፣ እና የDCPS ፍቃድ ያላቸው አፕሊኬሽኖችን እንደየክፍል ደረጃ እና ትምህርት ቤት ወይም አስተማሪ ጥያቄ መሠረት፣ እንደሚከተለው ይመድብላቸዋል:

- **ማግኘት/Access**: ወደ DCPS ስር ዓቶች እና ዲቫይሶች፤ ሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች - ለየግል-ባዘጋጁት ማስረጃዎች እና የሚስጥር-ኮዶች (passwords)ን - መጠቀም-አለባቸው።
- **ኢሜል:** በ9ኛ ክፍል እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች፣ የዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course)ን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ፣ የDCPS ኢሜል አካውንት ይሰጣቸዋል። በሌሎች ክፍሎች ውስጥ ለሚገኙ ተማሪዎች፣ እንደ DCPS ሠራተኛው ውሳኔ መሠረት፣ የዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course)ን በተሳካ ሁኔታ ካጠናቀቁ በኋላ፣ የDCPS ኢሜል አካውንት ሊሰጣቸው ይችል ይሆናል። የተወሰነ ዓይነት ጉደተኝነት ያላቸው ተማሪዎች፤ ፈተና የማግኘት እና የክፍል ውስጥ ማመቻቻዎችን በእነርሱ 'አይኢፒ (IEP)' ውስጥ እንደተዘረዘረው፤ ድምጽን ከፍ አድርጎ ማንበብ (Read aloud)ን እና የተደጋገመ ትዕዛዛትን፣ የጽሁፍ/textን የቀነሰ-የመነበብ ሁኔታን፣ ጽንሰ-ሃሳብን-ቀላል ማድረግን እና ሌሎች ማመቻቻዎችን አካትቶ ሊይዝ የሚችለውን በመጠቀም፤ የዲጂታል የዜግነት ኮርስ (Digital Citizenship course)ን ሊያጠናቅቁ ይችላሉ።
- አፕሊኬሽኖች (**Applications**): DCPS በተወሰነ ደረጃ ፈቃድ ያገኙ አፕሊኬሽኖችን ለሁሉም የDCPS ሠራተኞች እና ተማሪዎች እንዲጠቀሙ መንገድ ይሰጣል። የሠራተኞች የማግኘት-ፈቃድ የሚሰጠው እንደ ስራ ኃላፊነታቸው እና ለተወሰኑ አፕሊኬሽኖች/applications፣ በርዕሰ መምህሩ ጥይቄ መሠረት ነው። ለተማሪዎች የማግኘት ፈቃድ የሚሰጣቸው አፕሊኬሽኖች፣ ፈቃድ የተሰጣቸውን መጠቀሚያዎች ነው። በትምህርት ቤቱ እና በአስተማሪው ጥያቄ መሠረት፣ ተማሪዎች ፈቃድ ከተሰጣቸው መጠቀሚያዎች ውጪ ሌሎች አፕሊኬሽኖችን ማግኘት ይችሉ ይሆናል።
- **ምርቃት/Graduation ወይም አለመቀጠር/Unenrollment:** ከDCPS የተመረቁ ወይም ያልተመዘገቡ ተማሪዎች፤ የDCPS ቴክኖሎጂን ወይም ስርዓቶች/systemsን - አፕሊኬሽኖች (applications)ን እና የተቀመጡ ቁሳቁሶች (stored materials)ን ጨምሮ፣ የማግኘት መብት አይኖራቸውም።

5. የሚስጥር-ኮዶች (Passwords)

በሁሉም በDCPS-በተሰጠ ቴክኖሎጂ ላይ፣ በDCPS ፈቃድ-ባልተሰጠው ተጠቃሚ እንዳይጠቀመው ለመከላከል

---

[6] ከ'COPPA' ጋር ተገዢ-የሆኑ - ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባካችሁ - እዚህ ተመልከቱ https://www.ftc.gov/tipsadvice/business-center/guidance/complying-coppa-frequently-asked-questions.

## የተማሪ እና ሠራተኛ፣ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ የመጠቀሚያ ፖሊሲ

የሚስጥር ኮድ (Password) ለመካላከያነት ያስፈልጋል፣ እና ተጠቃሚዎች ወደ የትምህርት ቤት -ኮምፒውተሮች፣ ኔትወርኮች፣ እና የኦንላይን መጠቀሚያ-ዘዴዎች - በሚገቡ-ጊዜ (logging into በሚያደርጉ-ጊዜ)፣ ከDCPS የሚስጥር ኮድ (password) መስፈርቶችን በተከተለ-መልኩ መጠቀም ያስፈልጋቸዋል። ተጠቃሚዎች፣ የሚስጥር ኮድ (password)ን በመደበኛነት አዲስና-ማሻሻያ በማድረግ (updating) ሂደታቸው አንዱ-አካል ሆኖ፣ እነዚህን የDCPS የሚስጥር-መግቢያ ኮድ (password) መስፈርቶች እንዲያሟሉ ይጠየቃሉ።

ተማሪዎች እና ሠራተኞች - የሚስጥር የመግቢያ ኮዳቸውን (password) ወይም የሌላ የDCPS ተማሪን ወይም የሠራተኛ አባልን - በቅንነትም ሆነ ወይም ደግርሞ ፖሊሲውን በመጣስ ያወቁትን የሚስጥር ኮድ (password)ን - ከሌላ ጋር የማጋራት ፈቃድ የሌላቸው እና ሌላ የግል መረጃዎችን የሚጠይቁ፣ የኢሜል ማታለያዮች (email scams) ለማስወገድ የተቻለውን ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። እነዚህን ማታለያዎች (scams) እንዴት ማስወገድ እንደሚቻል እና ሌላ ቴክኖሎጂን በደህንነት-ለመጠቀም መልካም-የሆኑ ልምዶችን ለመማር፤ ተማሪዎች በዲጂታል ጥሩ-ዜግነት (digital citizenship) እና በኦንላይን የደህንነት-ጥበቃ ትምህርቶች ውስጥ እንዲሳተፉ - DCPS ይጠይቃል።

የዲጂታል ጥሩ-ዜግነት (digital citizenship) ትምህርቶችን አቀላጥፈው-ለማወቅ የማይችሉ - ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ተማሪዎች (Students with disabilities)፣ በእነዚህ የሚስጥር ኮድ (password) መስፈርቶች ውስጥ የሚካተቱ-አይሆንም።

የተከለከሉ ነገሮችን የመጠቀም ቅጣቶች፤ የኔትወርክ ማግኘት ግደባዎችን ወይም የአካውንቶች መሰረዝን ሊያስከትሉ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ ጥሰቶቹ ምናልባት ለተማሪዎቹ፣ በስነ ስርዓት እና/ወይም የሕግ እርምጃዎችን የሚያስከትሉ ሆነው፣ ለተወሰነ ጊዜ መታገድ፣ ማስወገድ፣ እና በወንጀለኛነት መከሰስን ይጨምራል።

6. ቴሌሄልዝ (Telehealth)/ቴሌሜዲሲን (Telemedicine) ማግኘት

የDCPS ሠራተኞች እና ተማሪዎች፣ የቴሌሄልዝ (telehealth) ክፍለጊዜዎችን በDCPS ዲቫይሶች ላይ ለማግኘት ይፈቀድላቸዋል። ምንም-እንኳን DCPS በቀጥይነት የቴሌሄልዝ (telehealth) ክፍለጊዜዎችን የመቆጣጠር ፍላጎት ባይኖረውም፣ የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች የመረጃ ስብስቡን (data)፣ በትምህርት-ቤት የተሰጡ ዲቫይሶች ላይ፣ ይህም በዲቫይሱ ሃርድ-ዲስኮች ላይ እንዲቀመጡ የተደረጉ ሌሎች የሕክምና መረጃዎችን ጨምሮ፤ እንዲፈትሹ እና የተማሪ እንቅስቃሴን እንዲቆጣጠሩ፤ የፌደራል ሕግ ይጠይቃል። የቀጥታ-ስርጨት የቴሌሄልዝ (telehealth) ክፍለጊዜ፣ ቁጥጥር አይደረግበትም። ሚስጢራዊነት ያላቸው የመረጃ-ስብስብ (data)፣ በዲቫይሶች ሃርድ-ድራቮች ላይ ተቀምጦ ከሆነ፣ ዲቫይሶቹ ወደ ዕቃ-ስብስብ (inventory) ሲመለሱ መረጃዎቹ ይጸዳሉ።

7. ቪዲዮ ኮንፈራንስ ማድረግ

የቪዲዮ-ኮንፈረንስ የሚካሄደው፤ የDCPS ሠራተኛ እና ተማሪዎች እርስ-በራሳቸው የቪዲዮ-ኮንፈራንስ ማድረጊያ አፕሊኬሽን (videoconferencing application)ን በመጠቀም፣ በዚያኑ-ጊዜ በሚሰራጭ ድምጽ እና እይታ (real-time sound and vision) ግንኙነት በማድረግ ሲያካሂዱ ነው። አስተማሪዎች እና ሠራተኞች፣ የቪዲዮ-ኮንፈረንሱን መቅዳት እና ለራሳቸው እና ለተማሪዎች በኋላ እንዲገኝ ለማድረግ ይችላሉ።

ሠራተኞች ስለ ግል-መረጃዎችን የሚገልጹ መረጃን ስለተማሪው በቪዲዮ-ኮንፈራንሱ ክፍለ-ጊዜዎች ጊዜ መግለጽ የለባቸውም።

ሠራተኞች እና ተማሪዎች፣ ማንኛውንም ተገቢ-ያልሆነ ባህሪይን ወይም አሳሳቢ የሆኑ ባህሪይን፤ በቪዲዮ-ኮንፈረንሱ

ወቅት - የDCPS ቢሮን ታማኝነት[7] በሚነካ ሁኔታ ሲፈጠሩ፣ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው። ሠራተኞች እና ተማሪዎች፣ የDCPS የተቀጣሪ ሠራተኞች መብቶች እና ኃላፊነቶች ፖሊሲ (DCPS Employee Rights and Responsibilities Policy)[8]ን፣ የማህበራዊ ሚድያ ፖሊሲ (Social Media Policy)[9]ን፣ እና በሠራተኛ-ተማሪ ግንኙነቶችን በተመለከተ ሌላ-ማንኛውም ተገቢ- የሆኑ ፖሊሲ፣ ደንብ፣ እና ሕግን - መከተል አለባቸው።

8. አርቲፊሻል ኢንተለጀንስ (Artificial Intelligence (AI)

ልክ እንደ ሁሉም ቴክኖሎጂ፣ ተማሪዎች እና ሰራተኞች 'AI'ን በኃላፊነት እና በስነ-ምግባራዊ መንገድ መጠቀም ይጠበቅባቸዋል። የ'AI' መሳሪያዎች፣ በተማሪዎች እና በሠራተኞች - እንደ ማሟያ እንጂ ለመማር ምትክ መሆን ጥቅም-ላይ መዋል የለባቸውም። በ'ዲጂታል ጥሩ-ዜግነት (Digital Citizenship)' እና 'ለAI-በልዩ-ሁኔታ የሚሰጡ ኮርሶች' አማካኝነት ስለአላቸው-ጥቅሞች እና አደጋዎች፣ DCPS ለተማሪዎች ትምህርት ይሰጣል።

ምንም-እንኳን በሌሎች የዚህ ፖሊሲ ክፍሎች ውስጥ የተጠቀሱ ቢሆንም፤ ከዚህ በታች ያሉት የ'AI' አጠቃቀሞች በተለይ-የተከለከሉ ናቸው፣ እና ተጨማሪ ምርመራ-የሚያከትል ይሆናል:

- ማንጓጠጥ (Bullying) እና ትንኮሳ (Harassment): ተማሪዎች፤ ራሳቸውን ወይም ሌሎችን ሊጎዳ በሚችል መልኩ 'AI'ን እንዳይጠቀሙ ተከልክሏል። ሌሎችን ለማስመሰል/impersonate - ሚዲያዎችን ለመቆጣጠር፣ የ'AI' መሳሪያዎችን መጠቀም፣ የተከለከለ ነው።
- የሌላን-ስራ የራስ አድርጎ ማቅረብ (Plagiarism) እና ማጭበርበር (Cheating): ተማሪዎች፤ በ'AI' የመነጨ ስራን እንደ መጀመሪያ ስራቸው እንዳያቀርቡ ወይም ለፈተና-መልስ ለመስጠት፣ ለመፈተን እና ለሌላ የቤት-ስራ ጥያቄዎች (በአስተማሪያቸው ይህን እንዲያደርጉ ካልታዘዙ-በስተቀረ) መልስ-ለመስጠት 'AI'ን መጠቀም የተከለከለ ነው።

ከDCPS አስተማማኝ እና አወንታዊ የትምህርት ቤቶች ፖሊሲ (Safe and Positive Schools Policy)፣[10] ጋር ተስማሚ-በሆነ ሁኔታ፤ ሠራተኞች፣ ከሚፈቀዱ የዲሲፕሊን ምላሾች ገደብ ውስጥ - ከትንሹ በመጀመር ወደ ከፍተኛ-ደረጃ በሆነ መልኩ ከባድ ተገቢ ምላሽ ላይ፣ የስነ-ስርዓት ምላሽ-መስጫዎችን (disciplinary responses) መተግበር አለባቸው። ይህ የገደብ-ስፋት፣ እንደገና-ስራውን ከማስገባት እስከ የውጤት-ደረጃን መቀነስ ዕድልን ለመስጠት የተለያየ-ሊሆን ይችላል።

a. ለሠራተኛ የ'AI' አጠቃቀም፣ ተጨማሪ ከግምት-ውስጥ የሚገቡ ነገሮች

DCPS፣ ፈቃድ-ያለው የ'AI-enhanced tools'ን ለተማሪዎች መማር ዝርዝሩን በመጠበቅ የሚይዝ እና፣ የእነዚህን መሣሪያዎች በትክክለኛው መንገድ ጥቅም-ላይ መዋልን ለመደገፍ የሙያ-ማሳደርጊያ ስልጠናን ይሰጣል። አስተማሪዎች እና የትምህርት ቤት መሪዎች - በDCPS 'EdTech' ቡድን ከተዘረዘሩት ዝርዝር ውጭ የ'AI' መሳሪያን ለመጠቀም የሚፈልጉ-ከሆነ፤ በ'EdTech' ቡድን የተቀመጡትን መመዘኛዎች ማሟላት አለባቸው እና ከመግዛታቸው እና በክፍል ውስጥ ወይም በክፍል-ስራዎች (assignment) ላይ ከመጠቀማቸው አስቀድሞ - የ'AI' መሳሪያ ማጽደቂያ ቅጽ/AI Tool Approval Formን ማስገባት አለባቸው። እነዚህ መመዘኛው (criteria) እና ቅጹ፣ በ'EdTech SharePoint' ድህረ-ገጽ ላይ በዚህ ላይ ይገኛል https://dck12.sharepoint.com/sites/DCPSEdTechInformationResources።

---

[7] የሃቀኝነት ቢሮ (Office of Integrity) - የኦንላይን የመመራት (Referral) ቅጽ - እዚህ የሚገኘውን በመሙላት https://dcps.dc.gov/page/office-integrity ወይም በዚህ-ኢሜል በማድረግ dcps.cio@k12.dc.gov ማግኘት-ይቻላል።

[8] በ https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies ላይ የሚገኝ።

[9] በ https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies ላይ የሚገኝ።

[10] በ https://dcps.dc.gov/publication/safe-and-positive-schools-policy ላይ የሚገኝ።

በ‘AI’ የመነጨ ይዘት፣ ስህተቶችን ወይም አድሎዓዊ ጉዳዮችን ሊይዝ ስለሚችል፤ ሠራተኞች የታመኑ-ምንጮችን በመጠቀም፣ የማንኛውም በAI-የተሰራ ይዘት እውነተኛነት ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። የ‘AI’ ግንኙነቶች/communicationsን ለማድረግ ጥቅም-ላይ በሚውል ጊዜ፤ እንደ - ለወላጆች ኢሜይሎችን ማዘጋጀት - ባለው ላይ፣ ቋንቋው ሙያዊ-ብቃት እንዳለው እና ከስህተት እና ከአድልዎ ነፃ-የሆነ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው። ሠራተኞች፤ ከመጠቀማቸው-በፊት፣ ሁሉንም በ‘AI’ የመነጨ ይዘትን መገምገም እና በትኩረት ማጤን አለባቸው።

### C. ቴክኖሎጂ (ኮምፒውተሮችን፣ ላፕቶፖችን፣ ታብሌቶችን ጨምሮ)

1. የዲቫይስ እርዳታ (Device Support)

DCPS መሠረታዊ የሆኑ፣ የመጫን (installation)፣ የማቀናበር (synchronization)፣ እና የሶፍትዌር እርዳታ/software supportን፤ ለDCPS- ቴክኖሎጂ ይሰጣል። እነዚህ ዲቫይሶች፣ የሶፍትዌር አዲስ እና ማሻሻያዎችን ለመጫን እና/ወይም ለዕቃ ክምችት ቆጠራ (inventory) ሲባል፣ በመደበኛ ሁኔታ ከDCPS ኔትወርክ ጋር መገናኘት አለባቸው። ሁሉም ከDCPS- ለተሰጠ ቴክኖሎጂ፤ በሚጠፋ ወይም በሚሰረቁ ጊዜ - ያልተፈቀደ-አጠቃቀምን ለመከላከል እንዲያስችል፣ በሚስጥር ኮድ (Password) የተጠበቀ፣ መሆን ያስፈልገዋል።

2. ጉዳት-ሲደርስ (Damage)፣ ሲጠፋ (Loss)፣ ሲሰረቅ (Theft)

ሠራተኞች፣ ለDCPS ቴክኖሎጂ ታማኝ አገልጋዮች የሆኑ እና በቸልተኝነት በንብረቶች ላይ ለሚደርሱ ጉዳቶች፣ ጥፋት ወይም ስርቆት ምክንያት የገንዘብ ኃላፊነት አለባቸው። የቸልተኝነት ምሳሌዎች የሚጨምሩት፣ ነገር ግን በእነዚህ ብቻ ሳይወሰኑ እንደ:

- የDCPS ቴክኖሎጂ-የሆነውን - በተሽከርካሪ ወይም ሌላ ቦታ በመተው፣ በሙቀት፣ በብርድ ወይም በእርጥበት ምክንያት ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ፤
- መጠጦችን ወይም ምግብ በማፍሰስ - ጉዳት-ማድረስ፤ ወይም
- የDCPS ቴክኖሎጂን ብቻውን-በማስቀመጥ ወይም ጥበቃ በሌለው ቦታ በመተው እንዲሰረቅ ማድረግ።

የDCPS የሠራተኛ አባል፣ በDCPS ‘IT’ ቡድን የተመደበላቸውን መሳሪያ ብቻ መጠቀም አለባቸው፤ እና ለሌሎች በአሁኑ-ጊዜ ያሉ እና ለቀድሞ-ሠራተኞች የተመደቡ መሳሪያዎችን፣ መውሰድን ወይም መጠቀምን ይከለክላል።

ዲቫይሱን ከጉዳት፣ ከመጥፋት፣ ወይም ከመሰረቅ ለመከላከል፣ ተማሪዎች ተገቢ-የሆነውን እርምጃ ሁሉ - መውሰድ አለባቸው። ተማሪዎች ላደረሱት ጉዳት የሚደረገው የስነ ስርዓት ምላሾች፣ የDCPS የስነ ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎችን በተከተለ ሁኔታ ይወሰናል። ይህ የክትትል-ምርመራ፤ ተማሪው ስለ ዲቫይስ እንክብካቤ፣ ዕድሜን እና ማንኛውንም ተዛማጅ-የሆኑ ጉዳተኝነትን ጨምሮ፤ መገንዘብ በመቻሉና አለመቻሉ ላይ በሚያደርሰው-ተጽዕኖ ላይ ያሉትን ምክንያቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል። *ከግዴለሽነት ወይም ሆን ተብሎ ከተደረገ የጥፋት ጉዳት ማድረስን* ጨምሮ፣ ነገር-ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ የቀረቡ ምሳሌዎች:

- በዲቫይሱ ላይ በማይጠፋ ማርከር (permanent marker) በመጠቀም መሳል፣ ቃላቶችን/ምስሎችን ስለታማ በሆኑ ነገሮች በመፋቅ መፃፍ ወይም መሳል፣ ወይም በዲቫይሱ ላይ በእንስሳት የተነከሰበት ምልክቶች (animal bite marks)፤
- በተለያዩ ቦታዎቹ ላይ፣ በሚከተሉት ምክንያት ጉዳት ሲደርስበት፤ ዲቫይሶቹ በሚገባ ስላልተያዙ ወይም እንክብካቤ-ባለመደረጉ ምክንያት (ለምሳሌ፤ ስክሪኑ መሰንጠቅ፣ ኪቦርዱ (keyboard) መበላሸት፣ ቁልፎቹ (keys) ተነቅሎ ሲጠፋ፣ ወይም የላፕቶፑ ሽፋን የተመታ መሆኑን በተለያዩ ቦታዎቹ ላይ ሲታይ ወይም ላፕቶፕ/ታብሌት ተገነጣጥሎ በተለያየ-ቁርጥራጮች ሲመልሱ)፤

- ሃይለኛ የሆነ ጉዳት፣ ስለታም ነገር በመጠቀም ወይም ከባድ እቃ(ዎችን) በመጠቀም የተነሳ ጉዳት ሲደርስ፣ ወይም በእቃ(ዎቹ) በላፕቶፑ USB ላይ ወይም የኤሌክትሪክ መሰኪያው ላይ ተጭኖት ጉዳት ሲደርስበት፤
- ዲቫይሱ ሙሉ-ለሙሉ በውሃ ውስጥ ወይም በፈሳሽ-ነገሮች ውስጥ ተነክሮ ነበር፤ ወይም
- ተማሪው፣ በአንድ የትምህርት ዓመት ውስጥ በሶስት (3) ወይም ከዚያ በላይ ዲቫይሶች ላይ ጉዳት ካደረሰ፤ ተደጋጋሚነት-ያለው የጉዳት ሁኔታ (Repeated pattern of damage) ሲደርስ።

በግዴለሽነት ወይም ሆን-ተብሎ ከተደረገ የጥፋት ጉዳት በማድረስ ላይ ምክንያት-ሆኖ - በዲቫይሶቹ ላይ ጉዳት ሲደርስ፣ ለተማሪዎች የስነ-ስርዓት መቅጫ ምላሾቹ፣ በ'DCPS Safe and Positive Schools Policy'[11] ስር የስነ-ምግባት ደንቦች እና ሕግ፣ እና ተቀባይነት ያለው የመጠቀሚያ ፖሊሲ (Acceptable Use Policy) - የሚወሰን ይሆናል።

ከተለመደ የማርጀት የተነሳ (wear and tear) ወይም ሆን-ተብሎ ያልሆነ አደጋዎች ከሚደርሱ ጉዳቶች፣ ተማሪዎች ላይቀጡ ይችሉ ይሆናል። *ከተለመደ የማርጀት የተነሳ (wear and tear)* የተነሳ-የጥፋት መድረስ ምክንያት የተፈጠሩ፤ እነዚህ ምሳሌዎችን ጨምሮ፣ ነገር ግን በነዚህ ብቻ ሳይወሰን:

- ከኪቦርዱ (keyboard) ላይ አንድ ቁልፍ (key) ወይም ቁልፎች ሲጠፉ፤
- በድንገት በመውደቁ-ምክንያት፣ በስክሪኑ (screen) መሰንጠቅ-ሲኖር፤
- ዲቫይሱ በድንገት በወደቁ ምክንያት የተፈጠረ ሊሆን የሚችል፣ እንደ በስክሪኑ የጎን ማዕዘን/ኖች ላይ በሆነው - በዲቫይሱ አነስተኛ-ክፍል ላይ ተለይቶ የሚታይ ጉዳት፤
- በኪቦርዱ (keyboard) ላይ፣ በድንገት ፈሳሽ ነገር ሲፈስበት፣ ወይም
- በኃይል-መጨመር ምክንያት የሚከሰት ብልሽት።

የDCPS ቴክኖሎጂ ከጠፋ፣ ከተሰረቀ ወይም ከተበላሸ፤ ተማሪዎች - ለአስተማሪ ወይም ለትምህርት ቤት መሪ ማሳወቅ አለባቸው፤ ሠራተኞች ደግሞ ለተቆጣጣሪዎቻቸው እና ለDCPS የቴክኖሎጂ የግንኙነት-አገልግሎት ሰጪ ሰው (point of contact) ማሳወቅ አለባቸው። DCPS የጠፋውን ንብረት ለማግኘት እና ዲቫይሱ የያዘውን ማንኛውንም መረጃ በደህንነት እንደተጠበቀ ለማረጋገጥ ተገቢውን እርምጃዎች ሁሉ ይወስዳል። DCPS፣ እንደጠፋ ወይም እንደተሰረቀ የተጠቆመውን ዲቫይስ ወይም ወደ ትምህርት ቤት ያልተመለሱትን ዲቫይሶች በርቀት እንዳይሰሩ ለማድረግ - ያለበትን ቦታ በማግኘት - የቦታ መጠቆሚያ ሶፍትዌርን (location tracking software)ን በዲቫይሱ ላይ ማስቀመጥን ሊመርጡ-ይችላሉ። የተበላሹ/Damaged ዲቫይሶች - ወደ የDCPS 'IT' ቡድን (AssetAdmin@k12.dc.gov) መመለስ-ያለባቸው እና፣ በተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ ወይም በሠራተኞች መጣል/መወገድ የለባቸውም። ተተኪ-ከመሰጠቱ በፊት፣ በDCPS IT ቡድን እና በOCTO፤ በመጀመሪያ ምርመራ-በዲቫይሱ ላይ መደረግ አለበት።

---

[11] በ https://dcps.dc.gov/page/dcps-policies ላይ የሚገኝ።

3. ለአንድ ሌሊት (Overnight) ወይም በቤት ውስጥ (At-Home) በተማሪዎች መጠቀም

የDCPS ትምህርት ቤት ሠራተኞች፤ ለአንድ-ሌሊት (overnight) ወይም በቤት ውስጥ (at-home) መጠቀሚያ የሚሆን የDCPS ዲቫይሶችን፣ ከቻንስለሩ ወይም ከ'IEP' ቡድን - ተገቢ-ሆኖ በሚገኝ-ጊዜ እና ከፖሊሲው ጋር በሚሄድ ሁኔታ - ውሳኔ ከተሰጠው፤ ለተማሪዎች ሊሰጡ ይችላሉ። የDCPS ተማሪዎች እና ወላጅ/አሳዳጊ፤ ከዚህ ጋር አባሪ የሆነው የተማሪ 'Acceptable Use Agreement'ን፣ (አባሪዎቹ/Appendicesን ተመልከቱ) - በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ለአንድ ሌሊት-አሳድረው (overnight) ለመጠቀም ዲቫይስ ከመመደቡ በፊት፤ መፈረም አለባቸው። የDCPS ትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ በተማሪ ዲጂታል የግላዊነት ህግ ጥበቃ (Protection of Student Digital Privacy Act) መሰረት የግላዊነት መስፈርቶችን ማክበር አለባቸው፣ እና ወላጆች እና ተማሪዎች እነዚህ መሳሪያዎች በDCPS ሠራተኞች ክትትል ሊደረግባቸው እና ሊታዩ-እንደሚችሉ ማወቅ አለባቸው።[12]

አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology)፤ የተማሪው የIEP ቡድን፣ ከDCPS አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology) ቡድን ጋር ትብብር-በማድረግ፤ ተማሪው እነዚህ እገዛዎች ትምህርታዊ ስራዎቹን በመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ለማጠናቀቅ (ለምሳሌ የቤት ስራ፣ ግንኙነቶችን ለማድረግ) እንደሚያስፈልጉት ከወሰኑ፤ ተማሪው ወደ ቤት ሊወስድ ይችላል። ቴክኖሎጂን በመኖሪያ-ቤት ውስጥ በመጠቀም ጊዜ፣ ቴክኖሎጂን በትምህርት ቤት ውስጥ በሚጠቀሙ ጊዜ ወይም ከተጠቀሙ የሚጠቀሙትን ዓይነት - ሁሉንም የDCPS ፖሊሲዎችን ተማሪዎች መከተል አለባቸው። ስለ አጋዥ-የሆኑ ቴክኖሎጂ (assistive technology) ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባካችሁ - የDCPS አጋዥ የሆኑ ቴክኖሎጂ (Assistive Technology) ድህረ ገጽን ተመልከቱ[13] ወይም በDCPS.AssistiveTech@k12.dc.gov ወይም የተማሪውን የ'IEP' ቡድንን አነጋግሩ።

### D. ባሕሪያት (Conduct) እና ተቀባይነት ያለው መጠቀሚያ

የDCPS ኔትወርክ እና የDCPS ቴክኖሎጂን በመጠቀም፣ ሠራተኞች - ሁሉንም የዲሲ መንግስት (DC Government)፣ OCTO; እና የDCPS ደንቦችን፣ ፖሊሲዎችን እና መመሪያዎችን - ለመከተል ተስማምተዋል። ሠራተኞች እና ተማሪዎች - አላግባብ-አጠቃቀምን ወይም የፕሮቶኮሎች መጣሶችን፤ ለአስተማሪዎች፣ አግባብ ላላቸው ኃላፊዎች፣ አስተዳደሮች፣ ወይም ለማዕከላዊ አገልግሎቶች ተቀጣሪ-ሠራተኞች - አላግባብ አጠቃቀሙ ወይም ጥሰቱን[14] መድረሱን -እንዳወቁ፣ ወዲያውኑ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው።

ሠራተኞች እና ተማሪዎች፣ የDCPS ኔትወርክ ወይም የDCPS ቴክኖሎጂን፤ የሚከተሉትን-ጨምሮ - ኢንተርኔት ማግኘት፣ ኢንትራኔት(intranet)፣ የትብብር መሣሪያዎች (collaboration tools)፣ የጅምላ (bulk) መገናኛ መሳሪያ፣ ማህበራዊ ሚዲያ ወይም ኢሜል ለመጠቀም፣ ለመቅዳት፣ ለማጋራት፣ አፕሎድ ለማድረግ (upload)፣ ለመለጠፍ/post ለማድረግ፣ ሜል (mail)፣ ማሳያ፣ ማስቀመጥ ወይም ሌላ ማስተላለፊያ መንገድን፣ በማንኛውም ይዘት፣ መገናኛ ወይም መረጃን፣ መጠቀም የለባቸውም:

1. ጥላቻ ያለበት፣ መነዝነዝ፣ ማስፈራራት፣ አጥፊነት፣ ወይም ስም ማጥፋት ነው፤
2. አጸያፊ ወይም በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በብሄራዊ አመጣጥ፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በግል አቋማዊ ገጽታ፣ ፆታዊ አመለካከት፣ በፆታ መለያ ወይም አገላለጽ፣ በቤተሰብ ሁኔታ፣ በቤተሰብ ኃላፊነቶች፣ በመማሪያ በታዎች፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ የዘር አመጣጥ መረጃ፣ በጉዳተኝነት፣ በገቢ ምንጭ፣ በቤተሰብ ውስጥ ባለ ወንጀል ሳቢያ ሰለባ የመሆን ሁኔታ፣ በመኖሪያ ወይም በንግድ ቦታ ሳቢያ፣ የሰለባ ወይም የሰለባው የቤተሰብ አባል መሆን – በቤት ውስጥ ሁከት፣ በወሲባዊ ጥቃት፣ ወይም በማሳደድ፤ እነዚህን ሁሉ መሠረት በማድረግ በሰው ላይ አድልዎ ማድረግ፤

---

[12] D.C. Official Code § 38-831.03(c) ተመልከቱ።

[13] በhttps://dcps.dc.gov/page/assistive-technology%E2%80%AF ላይ የሚገኝ።

[14] ሪፖርቶችን እና አቤቱታዎችን ፋይል ስለማድረግ - ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እካካችሁ 'Section V'ን ተመልከቱ።

3. ማንኛውንም የወንጀል ጥፋትን ማሴር ወይም ማስፋፋት፣ ወይም ለሲቪል ተጠያቂነት ማነሳሳት፣ በማንኛውም በስራ ላይ በዋለ ሕግ ስር፣ የU.S. የላኪ ቁጥጥር (export control) ሕጎች ወይም የU.S. ፓተንት (patent)፣ የንግድ ስያሜ (trademark) ወይም የቅጂ መብቶች (copyright) ሕጎችን ጨምሮ፤
4. ማንኛውም ጸያፍ ወይም ለወሲብ ክንውን (pornographic) የሚውል-ነገሮች የያዘ፣ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ነገር-ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፣ ማስተላለፍ፣ ማውጣት ወይም ወራዳ፣ ጸያፍ፣ ወይም የወሲባዊ ግልፅ ይዘት ያላቸውን ነገሮች የማሳየት ጥቅም ላይ ለማዋር መስራት ወይም መደገፍ፤
5. ሁከትን ለማነሳሳት በማሰብ፣ የግል ጥቃት ወይም አካላዊ ጉዳት ለማድረስ፣ ወይም ወይም ለመነዝነዝ፣ ለማስፈራራት ወይም ሌላ ግለሰብን ለማገድ በማሰብ መረጃዎችን በማዘጋጀት ለማነሳሳት ወይም ለማሰራጨት መሞከር፣
6. ቫይረስ፣ ትሮጃን ሆርስ (trojan horse)፣ ራንሳምዌር (ransomware) ወይም ሌላ ጉዳት የሚያስከትሉ ይዘቶች ያላቸው ወይም ተንኮል አዘል ኮድን የያዘ፣
7. ጀንክ ሜል (junk mail)፣ ፊሺንግ (phishing) ስፖም (spam) ወይም ፍቃድ የሌላቸውን ኢሜሎች ለማሰራጨት ማነሳሳት፣
8. የማንኛውም የሌላ ኮምፒውተር ወይም ኔትወርክ የደህንነት ጥበቃን መጣስ ወይም ያልተፈቀደ የማግኘት ዘዴን ወይም ማንኛውንም የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን የማክሸፍ ዘዴ ሙከራ በማድረግ ማነሳሳት፣
9. የሌላ የDCPS ኔትወርክ ተጠቃሚን አካውንት፣ ፋይሎች ወይም የመረጃ ስብስብ (data) ውስጥ መግባት፣ ወይም ፋይሎቻቸውን፣ የመረጃ ስብስቡን (data) ወይም የሚስጥር ቁልፎችን (passwords) መቀያየር፣
10. ማንኛውንም በሕይወት ያለ ወይም የሞተን ሰውን፣ ድርጅትን፣ ንግድን፣ ወይም ሌላ አካልን - አስመስሎ-መገኘት (Impersonate ማድረግ)፤
11. በDCPS ኔትወርክ ወይም ቴክኖሎጂ ላይ፤ ክንውኖቹን ማጣጣል፣ የደህንነት ጥበቃው ላይ አደጋን መፍጠር፣ ወይም ካልሆነ-ደግሞ ታማኝነትን ወይም ቀልጣፋ ክንውንኖቹ ላይ ማስፈራራት፣
12. የDCPS ኔትወርክን ወይም ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ፍቃድ ያለው ተጠቃሚ መከልከል፣
13. የDCPS ቴክኖሎጂን ወይም የDC ኔትወርክን ፍቃድ ካላቸው በላይ በሆነ ሁኔታ ማግኘት፣
14. ወደ DCPS የኔትወርክ ስርዓት - ባልተፈቀደ-ሁኔታ ወይም ሕገወጥ በሆነ መንገድ፣ ገብቶ መጠቀም፤
15. ሚስጢራዊ ወይም ድርጅታዊ የሆኑ መረጃዎችን፣ የተማሪ የመዝገብ መረጃን ጨምሮ፣ ካለፈቃድ ወይም ትክክለኛ የጥበቃ እርምጃዎች ሳይወሰዱ አሳልፎ መስጠት፣
16. በግላዊነት ሊለዩ የሚችሉ የተማሪ መረጃዎችን፣ ቪዲዮዎችን እና ፎተግራፎችን ካለፍቃድ ወይም ትክክለኛ የጥበቃ እርምጃዎች ሳይወሰዱ አሳልፎ መስጠት ወይም ማስተላለፍ፣
17. ስለተማሪዎች ወይም የDCPS ሠራተኛን ሚስጢራዊ የሆኑ መረጃዎች፣ የዲሲ ሕግን፣ የፌደራል ሕግን፣ ደንቦችን፣ ፖሊሲ ወይም መመሪያ በመጣስ ማጋራት፣
18. የDCPS ኢሜል አድራሻዎችን ወይም ማሰራጫ ዝርዝሮችን ይህንን ፖሊሲ ወይም ሌላ የDCPS ፖሊሲዎችን በሚጥስ ሁኔታ ማጋራት፤
19. ማንኛውም ዓይነት ውርርድን ወይም ቁማርን ማድረግ ወይም ማነሳሳት፣
20. ፈቃድ የሌለው ሶፍትዌር ወይም የሶስተኛ ወገን የአገልግሎት ዘዴን መጫን፣ ዳውንሎድ ማድረግ ወይም መጠቀም፣
21. ፍቃድ የሌላቸው ጨዋታዎች (games)፣ ፕሮግራሞች፣ ፋይሎች፣ የኤሌክትሪክ ሚዲያ፣ ወይም ለብቻው የቆመ አፕሊኬሽኖች (stand-alone applications)ን፣ በDCPS ኔትወርክ ላይ አደጋ ሊፈጥር የሚችሉ ነገሮች ከኢንተርኔት ማውጣት፣ ማሰራጨት፣ ዳውንሎድ ማድረግ እና መጠቀም፤
22. ፍቃድ በሌለው በማንኛውም ዓይነት የዕጣ-ቲኬት ማውጣት (raffles) ወይም የገንዘብ ማሰባሰቢያዎችን (fundraisers) ማስተዋወቅ ወይም መካፈል፣
23. በህብረት የሚሰሩ ፖሊቲካዊ (partisan political) እንቅስቃሴዎች ውስጥ፣ በማንኛውም ሁኔታ ማስተዋወቅ ወይም መካፈል፣
24. በውስጥ ፖለቲካ ወይም የምርጫ እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት ያለው ማኅበር ወይም ሌላ ድርጅቶችን

የሚወክል ተቀጣሪን በማንኛውም መንገድ ማስተዋወቅ ወይም ከእነርሱ ጋር አብሮ-መካፈል፣

25. በግል ንግድ፣ የሺያጭ ወይም ሌላ እንቅስቃሴዎችን፣ በግል ገንዘብ ማግኛነት መሰማራት፤
26. የሌላን-ተጠቃሚ የሚስጥር ቁልፎችን (passwords) ወይም የደህንነት ጥበቃ ዘዴ መረጃን በተመለከተ፣ ባልተፈቀደ-ሁኔታ ማሰራጨት፣
27. በDCPS ኔትወርክ ወይም ማንኛውም የትምህርት ቤቱ ዘዴዎች ላይ የሚገኝ የመረጃ ስብስብ (data) ላይ፣ በውሸት፣ በመነካካት ወይም ፈቃድ ያላገኘ ለውጦችን ማድረግ፣ መጨመር ወይም ማጥፋት፤
28. በDCPS ኔትወርክ ላይ የሚገኙ የመረጃ ስብስብን (data) ለግል ጥቅም ማግኘት ወይም መጠቀም፤
29. በቅድሚያ ከርዕሰ መምህሩ እና የተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ የፅሁፍ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር፣ ከስርዓተ ትምህርቱ ወይም በትምህርት ቤት-ድጋፍ የማያገኝ ከትምህርት ውጪ እንቅስቃሴዎች ጋር ግንኙነት የሌላቸው ማንኛውም እንቅስቃሴ ወይም ግንኙነት ማስተዋወቅ ወይም መሳተፍ፣
30. የተለየ የቴክኖሎጂ፣ አፕሊኬሽን ወይም የDCPS ኔትወርክ ዘዴ ላይ በልዩነት የሚሰራን የሚያገለግል የአጠቃቀም ውልን መጣስ፤
31. የትምህርት ቤትን ወይም የቢሮን ትክክለኛና ስርዓት የያዘ የአሰራር ዘዴን - ለማወክ መስራት፣
32. ሃክ በማድረግ (hacking) (ማለትም፤ በአለማቀፋዊነት በሕገወጥነት ወይም ካለፈቃድ መግባት መቻል) ወደ DCPS ኔትወርክ በመግባት ያልተፈቀደ መረጃን፣ ወይም የመረጃ የደህንነት ዘዴዎችን ካልሆነም ለማክሸፍ መካፈል፤
33. የማይፈለግ የወሲብ ንክኪ፣ ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ መገላለጥ፣ ወሲብን የሚጋብዙ ምስሎችን ማሰራጨት፣ ወይም ሌላ የወሲብ እንቅስቃሴዎችን ጨምሮ፤ ተገቢነት የሌለው የወሲብ ባህሪ ማሳየት፣ ወይም
34. ማንኛውንም በዚህ ፖሊሲ ወይም በሌላ ማንኛውም የDCPS ፖሊሲ ላይ የተከለከለ ነጥብን መጣስ።

ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ሌላ ተጠቃሚዎች - ከDCPS-የተሰጠ ዲቫይስን ወይም የDCPS ኔትወርክ መግቢያን (log-in) መረጃ፣ ከማንም ሌላ-ግለሰብ ጋር ማጋራት የለባቸው። የሌላ ሰውን ከDCPS የተሰጠ ዲቫይስን ወይም ከDCPS የተሰጠ የመግቢያ (log-in) ኔትወርክ መረጃን መጠቀም፣ ፍቃድ-የሌውን ተጠቃሚ ከDCPS የተሰጠ ዲቫይስን ወይም ከDCPS የተሰጠ የመግቢያ (log-in) ኔትወርክ መረጃን እንዲጠቀም ፈቀድ፣ ወይም ከDCPS የተሰጠ ዲቫይስን ወይም ከDCPS የተሰጠ የመግቢያ (log-in) ኔትወርክ መረጃን ለመጠቀም ፈቃድ ከሌለው ጋር እንዲጋራ በማድረግ ማመቻቸት ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መንገድ መጠቀም በጥብቅ የተከለከለ ነው።

### E. **የግል የሚዲያ ቴክኖሎጂ/Personal Media Technology**

ከቻንስለር ወይም ከተወካዮቻቸው የተሰጠ ግልጽ የጽሁፍ ፈቃድ-መስጫ ሳይኖር፤ በDCPS ኔትወርክ ላይ የተማሪ የግል ቴክኖሎጂን መጠቀም አይፈቀድም። DCPS የተማሪዎችን የግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች የመጠገን እና የደህንነት ጥበቃ የማድረግ ሃላፊነት የሌለበት እና ቢጠፋ ወይም ቢሰረቁም ምንም ኃላፊነት የለበትም። DCPS፣ OCTO፣ እና ሠራተኞቻቸው፣ በትምህርት ቤት ውስጥ ወይም በDCPS ኔትወርክ ውስጥ - የግል ኤሌክትሮኒክስ ዲቫይስን ለመጠቀም፣ ወይም ከDCPS ከተፈቀደው ድጋፍ-ከተሰጠው በድህረ-ገጽ መሠረት-ያደረገ ውጪ በDCPS ዲቫይሶች ላይ የግል ሚዲያ አካውንቶችን ለማግኘት፣ በግል ዲቫይሶች ላይ በጥቅም-ላይ ያሉ በDCPS-ፈቃድ-ያገኙ መተግበሪያዎች (applications)ን ለመጠቀም ለሚፈልጉ ተማሪዎች፤ የቴክኒካል እርዳታን እንዲሰጡ አይጠየቁም። ከዚህ በታች ባለው ክፍል በተገለጸው መሠረት ካልሆነ በስተቀር፣ የDCPS ኔትወርክን በሚጠቀሙ ጊዜ፣ DCPS በግል የኤሌክትሮኒክስ ዲቫይሶች ላይ የደህንነት ጥበቃ እርምጃዎችን ለማስፈጸም ሲባል እና የDCPS ፖሊሲዎችን ሲጥሱ የተገኙ ዲቫይሶች እንዲወገዱ ያደርጋል።

### F. **የተማሪ የግል ሚዲያ አካውንቶች እና ቴክኖሎጂ - ግላዊነት (Privacy of Student Personal Media Accounts and Technology)**

1. በትምህርት ቤት ልዩ-የሆነ የተማሪ የግል የሚዲያ አካውንት እና ቴክኖሎጂ ፐሊሲዎች (School-Specific Student Personal Media Account and Technology Policies)

ርዕሰ መምህራን፤ ትምህርት ቤታቸው 'ከተማሪ የግል ሚዲያ አካውንቶች እና የቴክኖሎጂ ዲቫይሶች (personal media accounts and technological devices) ጋር የተያያዙ ተጨማሪ ህጎች ካሉ፣ ለተማሪዎች እና ለወላጆች በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

2. አጠቃላይ የግል ሚዲያ አካውንቶችና የተማሪ የቴክኖሎጂ ዲቫይሶች ግላዊነት (General Privacy of Personal Media Accounts and Student Technological Devices)

በክፍል/Section IV.G.3 ውስጥ ካሉት በስተቀር፣ DCPS በተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪ-በሚሆን ላይ፣ የስነ-ስርዓት እርምጃ የመውሰድ፣ የማባረር፣ ያለመመዝገብ፣ ለማስገባት መከልከል፣ ወይም በስርዓተ ትምህርት ወይም ከትምህርት ውጪ ለሚካሄዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዳይካፈል መከልከልን ጨምሮ፣ ተማሪው ወይም የወደፊት-ተማሪው - የሚከተሉትን ለማድረግ ፈቃደኛ ስላልሆነ እርምጃ አይወስድም፣ ወይም እርምጃ ለመውሰድ አያስፈራራም:

- የተማሪን የግል ሚዲያ አካውንት/personal media account ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ለመክፈትና ለመጠቀም የሚያገለግል፤ የመጠቀሚያ ስም (username)፣ የሚስጥር ቁልፍ (password) ወይም ሌላ የአካውንት ማረጋገጫን አሳልፎ በመስጠት፣
- የተማሪን የግል ሚዲያ አካውንትን ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን፣ በትምህርት ቤት ተቀማጭ የሆነ ሠራተኛ በተገኘበት፣ በአካውንቱ ወይም በዲቫይሱ ውስጥ ያለውን የመረጃ ስብስብ (data)፣ በትምህርት ቤት ተቀማጭ የሆነው ሠራተኛ እንዲመለከተው ማስቻል፣

- የተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የተማሪውን የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን እንዲመለከቱ ሰዎችን ወደዝርዝሩ መጨመርና እንዲጠቀሙ መፍቀድ፤ ወይም
- ከተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ[15] ጋር ግንኙነት ያለውን ግላዊ አቀማመጦች (privacy settings) መቀየር።

DCPS፤ የመጠቀሚያ ስም (username)፣ የሚስጥር ቁልፍ (password) ወይም ሌላ የአካውንት ማረጋገጫ መንገድን፣ በተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ አማካኝነት፤ ሕገወጥነት በሌለው መንገድ ሳያስበው ካገኘ፣ DCPS የሚከተለውን ያደርጋል:

- የተማሪውን ወይም የወደፊት ተማሪውን የሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ ተጠቅሞ መረጃዎችን ለማግኘት አይጠቀምም፤
- መረጃዎቹን ከማንም ጋር አለማጋራት፣ እና
- ወዲያውኑ ወይም ልክ እንደተቀበሉ፣[16] መረጃውን ማጥፋት።

በዚህ ክፍል፣ የሚከተሉት DCPSን ምንም አይከለክለውም:

- ስለተማሪው ወይም የወደፊት ተማሪው፣ በግልጽነት የተቀመጠ መረጃን ማግኘት፣
- ተማሪውን ወይም የወደፊት-ተማሪውን፣ ከግል ሚዲያ አካውንቱ ወይም ቴክኖሎጂ ዲቫይስ፣ ተግባራዊ ከሆኑ ሕጎች ወይም የDCPS ፖሊሲዎች፣ ጋር ተገዢ ለመሆን፣ ከፖሊሲ መስፈርቶቹ ጋር አብሮ የሚሄድ ጥያቄን ማቅረብን ተከትሎ፣ የተወሰኑ ይዘቶችን በፍቃደኝነት እንዲያጋራ መጠየቅ፤
- ተማሪውን ወይም የወደፊት ተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንቱ ወይም የቴክኖሎጂ ዲቫይሱን በትምህርት ቤት ሰዓት ወይም በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ እያለ እንዳይጠቀም ወይም እንዳይሰራበት መከልከል፣
- የDCPS ኔትወርክ አጠቃቀም ላይ ክትትል ማድረግ፣ ወይም
- ወደ DCPS ኔትወርክ ወይም DCPS ቴክኖሎጂ[17] ያለውን የተማሪ የማግኘት እድል፣ በሙሉ ወይም በከፊል መሻር።

### 3. በግል ሚዲያ አካውንቶች እና የተማሪ ቴክኖሎጂ - ግላዊነት ላይ የተለዩ ሆነው ያሉ-ነገሮች (Exceptions to Privacy of Personal Media Accounts and Student Technology)

የDCPS ሠራተኞች፣ የተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል የቴክኖሎጂ ዲቫይስን ፍተሻ-ሊያደርጉ (search) ወይም ከተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጅ ዲቫይስ በሚከተሉት የመመሪያ ጥሰቶች ወይም ለህይወት ወይም ለደህንነት አደጋ ሊደርስ የሚችል መረጃው - እንዲያወጣ ተማሪውን ሊያስገድድ ይችላል።

#### a. የፖሊሲ ጥሰቶች

የDCPS ሠራተኛ የተማሪውን የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ሊፈትሽ (search ለማድረግ) የሚችልበት ወይም ከተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስ ውስጥ የመረጃ ስብስብን (data) እንዲያቀርብ - ተማሪውን ሊያስገድድ የሚችለው፣ ተማሪው የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ተጠቅሞ ወይም በመጠቀም፣ የDCPS ፖሊሲን ለመጣስ እገዛ ያደረገ ድርጊት አድርጓል የሚል፣ የDCPS ሠራተኛው ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ ካለው እና የግል ሚዲያ አካውንት ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይሱ፣ ለተጠረጠረው

[15] D.C. Official Code § 38-831.04(a).
[16] D.C. Official Code § 38-831.04(b).
[17] D.C. Official Code § 38-831.04(e).

ጥሰት[18] ምስክር የሚሆኑ ይዘቶች አለው - በሚል ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ ካለው ይሆናል።

ይህን መሰሉን ፍተሻ ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ ተማሪው የመረጃ ስብስቡን (data) እንዲያቀርብ ማድረጉ፣ ከመከናወኑ በፊት፣ የDCPS ሠራተኛ የሚከተሉትን ማድረግ አለበት:

- ፍተሻውን ወይም እንዲያቀርቡ ማድረግን ያነሳሳውን ተገቢነት ያለውን ጥርጣሬን በሰነድነት መመዝገብ፣ እና
- የተጠረጠረውን ጥሰት - ለተማሪው እና ለተማሪው ወላጅ/አሳዳጊ ማሳወቅ እና፣ የሚፈለጉትን መረጃዎች ወይም ይዘቶች ፍተሻ-እንዲደረግላቸው ወይም ወይም ተማሪው እንዲያቀርብ ይገደዳል።[19]

ይህን ማስታወቂያ በመጠባበቅ ላይ እያለ፣ የቅድመ-ማስታወቂያ የመያዣ ጊዜው ከ48 ሰዓታት ካልበለጠ እና የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይሱ በተጠበቀ የDCPS ንብረት ውስጥ ከተቀመጠና በቅድመ-ማስታወቂያ የመያዣ ጊዜው[20] ውስጥ ጥቅም ላይ ካልዋለ ብቻ፣ መረጃዎች እንዳይሰረዙ ለመከላከል፣ DCPS የተማሪውን የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይስን ሊወስደው ይችላል።

የፍተሻው ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ማቅረብ ሁኔታው ሊወሰን የሚችለው፣ የመረጃ ስብስቡ (data) ከተገኘበት አካውንት ወይም ከዲቫይስ ወይም ጥሰቱ ተከናውኖበታል-ተብሎ ከተጠረጠረበት የዲቫይስ ይዘቶች የማረጋገጫ ምስክሮችን ለማግኘት ሲባል፣ ማንም-ሰው ሊያባዛ፣ ሊያጋራ፣ ወይም የመረጃ ስብስቦችን (data) ማስተላለፍ የማይችለው ከዚህ ፍተሻ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ማቅረብ ከተደረገው ጥሰት ጥርጣሬ ጋር ተያያዥነት በሌለው ሁኔታ ፍተሻውን[21] ካነሳሳ ይሆናል።

b. በቅርብ ሊከሰት የሚችል የሕይወት ወይም የደህንነት ስጋት

የDCPS ሠራተኛ፣ በቅርብ ሊከሰት የሚችል የሕይወት ወይም የደህንነት ስጋት[22] ካለ ምላሽ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፤ የተማሪውን የግል የሚዲያ አካውንቱን ወይም የግል ቴክኖሎጂ ዲቫይሱን መፈተሽ ወይም ከተማሪው የግል የሚዲያ አካውንቱ ወይም የግል የቴክኖሎጂ ዲቫይሱ አስገድዶ ሊወስድ ይችላል።

የማንኛውም ፍተሻ ስፋት የሚወሰነው ወይም አስገዳጅ በሆነ ሁኔታ የማቅረብ የሚከናወነበው፣ በዚህ ዓይነቱ ሁኔታ እና DCPS፣ የፍተሻ ወይም በአስገዳጅ ሁኔታ ማቅረብን በተጠየቀበት በ72 ሰዓታት ውስጥ ለተማሪው እና ለተማሪው ወላጆች፣ ፍተሻውን እና መረጃውን ማግኘት[23] ያስፈለገበትን ትክክለኛውን ስጋት በጽሁፍ ዝርዝር-መግለጫ ይሰጣል።

## V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚፈለጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተማሪዎች እና ሠራተኞች በዚህ በተቀረጸው ፖሊሲ መስፈርቶች መገዛት አለባቸው። አፈፃጸሙን ለመደገፍ፣ የሚፈለጉትን እንቅስቃሴዎች እና የጊዜ-አቀማመጥን በዓመታዊ አሰራሩ መሠረት፤ ሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ፣ ከርዕሰ መምህራኖች ይጠበቅባቸዋል። የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና በታዎችን መጎብኘት

[18] D.C. Official Code § 38-831.04(c)(1)(A).
[19] D.C. Official Code § 38-831.04(c)(1)(B).
[20] D.C. Official Code § 38-831.04(d).
[21] D.C. Official Code § 38-831.04(c)(1)(C)-(D).
[22] D.C. Official Code § 38-831.04(c)(2)(A).
[23] D.C. Official Code § 38-831.04(c)(2)(B)-(C).

(እንደ አስፈላጊነቱ) - እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት ተጠናክሮ ይካሄዳል። ይህ ማዕቀፍ (framework)፣ ሁላችንም በአንድነት ቀጣይነት ያለው ማሻሻያዎችን እና አለመገዛትን-የሚከላከል ዘዴን እንድንገነባ ያረጋግጥልናል። ቁልፍ ለሆነ መመሪያ እና እርዳታን-ከጥያቄዎች፣ ከስልጠና ወይም ከማስፈጸም ጋር ለማግኘት-ከፈለጉ፣ እባክዎን dcps.dc.gov ጎብኙ።

DCPS፤ እያንዳንዱን ተማሪ፤ በፍሀታዊ-እኩልነት፣ የላቀ-በላጭነት ባለው አሰራር፣ በግልጽነት፣ እና ተጠያቂነት ባለው-ሁኔታ ለማገልገል - ቁርጠኝነቱን-ያሳያል። ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ጥሰቶች ናቸው ተብሎ የታመነባቸው ነገሮች ሪፖርት ለማድረግ፣ ይህን  ትዕዛዝ መስጫ፣ የሃቀኝነት ሹም ቢሮን ለማነጋገር፤ የኦንላይን-መምሪያ (Online Referral) ቅጽን[24] በመሙላት ወይም ወደ dcps.cio@k12.dc.gov. ኢሜል መላክ።

[24] በ https://dcps.dc.gov/page/office-integrity. ላይ የሚገኝ

## አባሪዎች/APPENDICES

የሚከተሉት ሰነዶች እንደ አባሪዎች/appendices ሆነው ተካትተዋል:

- የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም ስምምነት/Student Technology Responsible Use Agreement፤
- የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም የስምምነት እውቅና-መስጫ ቅፅ/Student Technology Responsible Use Agreement Acknowledgement Form፤ እና
- ሠራተኛ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም የስምምነት እውቅና-መስጫ ቅፅ/Staff Technology Responsible Use Agreement Acknowledgement Form።

# የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም ስምምነት

**እንደ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የሚጠብቀም-ሰው:**

**A. የእኔን የDCPS ዲቫይሴን ክብር-በመስጠት፣ እንዳይወድቅ ጥንቃቄ በማድረግ እንከባከባለሁ።**

- ❑ የDCPS ዲቫይሴን፣ ስለመፈተሽ እና ስለመመለስ፣ የትምህርት ቤቱን ደንቦች እከተላለሁ።
- ❑ የDCPS ዲቫይሴ የተበላሸ ከሆነ ወይም በትክክል የማይሰራ ከሆነ፣ ወዲያውኑ ለአስተማሪ ወይም ለሠራተኛ አባል ሪፖርት አደርጋለሁ።
- ❑ በማልጠቀምበት-በማንናውም ጊዜያት ውስጥ፣ የእኔን ዲቫይስ በቤት-ውስጥ በተጠበቀ-በታ ውስጥ ተጠብቆ-እንዲቆይ አደርጋለሁ።

**B. የግል መረጃዬን (personal information)ን እጠብቃለሁ።**

- ❑ የእኔን የDCPS ዲቫይሴን - የተጠቃሚ ስም (username)ን፣ ወይም የሚስጥር ኮድ (password )ን - (የቅድመ ልጅነት ውስጥ/early childhood የምማር-ካልሆንኩ በስተቀረ ወይም የእኔን-አካውንት ለመጠቀም እርዳታ የሚያስፈልገኝ ተማሪ ካልሆንኩ-በስተቀር) ለማንም አላጋራም።
- ❑ በDCPS Office365 OneDrive ውስጥ ሁሉንም ስራዬን እንዲቀመጥ (save) የማደርግ፣ እና ስራዬን ስጨርስ - ከአካውንቶቼ እና ፕሮግራሞቼ (log out በማድረግ) እወጣለሁ።
- ❑ ሌላ ሰው አካውንቴን እንደተጠቀመ ከገመትኩኝ ወይም ካወኩኝ፣ ለአስተማሪውዬ ወዲያውኑ እነግራለሁ።

**C. ዲቫይሴን፣ ለትምህርት ቤት ስራ ብቻ - እጠቀማለሁ።**

- ❑ አስተማሪዬ ለመጫን ፈቃድ-ከሰጡኝ ብቻ፣ ሶፍትዌር/software፣ አፖች/apps፣ የ'browser extensions' ወይም የሚዲያ ፋይሎችን - ዳውሎድ/download፣ መጫን/install ወይም መጠቀምን ብቻ-እችላለሁ።
- ❑ ተገቢ-ያሆሆኑ፣ አፀያፊ፣ ወይም ሕገ-ወጥ የመረጃ-ምንጮችን - አስወግዳለሁ። በኦንላይን ላይ አግባብነት-የሌላቸው ነገሮችን ካየሁኝ፤ ወዲያውኑ ወደ አስተማሪው ወይም የሠራተኛ አባሉ ሪፖርት-አደርጋለሁ።

**D. የእኔን - [የዲጂታል ጥሩ-ዜጋ መሆን (digital citizenship)](#) ችሎታዎቼን እጠቀማለሁ፣ እና ሰዎችን በመልካምነት እንከባከባለሁ።**

- ❑ ክብር-ያላቸውን እና ተገቢ-የሆነ ቋንቋን እጠቀማለሁ።
- ❑ የሌሎችን ስራ በትክክል እጠቅሳለሁ እና የራሴ-አስመስዬ አልሰራም።
- ❑ በኦንላይን ላይ መረጃዎችን ከማጋራቴ በፊት፣ የመረጃውን ትክክለኛነት አረጋግጣለሁ።
- ❑ ሌሎችን በማያንጓጥጥ ወይም ጥቃት-በማይፈጥር ሁኔታ፣ እና የትምህርት ቤት ስራን የራስ-አስመስሎ በማያቀርብ ወይም በማያጭበረብር ሁኔታ፣ ኃላፊነት-ባለው እና ባህላዊነት በሚያከብር መንገድ - የሁሉንም ግላዊነት/privacy በሚያከብር-ሁኔታ ' Ai'ን እጠቀማለሁ።

**ኃላፊነት-የሌለው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም የሚያመጣው ውጤቶች/Outcomes for Irresponsible Technology Use**

የDCPS ኔትወርክን ለማግኘት የሚያስችል-መንገድን፤ ወይም በDCPS ተማሪ የስነ-ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎች (DCPS student discipline regulations and policies) ስር - የDCPS ቴክኖሎጂን ለረዘም-ያለ የጊዜ-ወቅት ለማግኘት-የመቻል አቅምን ታጣላችሁ። በተወሰኑ-ሁኔታዎች ስር፣ የDCPS ሠራተኛ - ሁሉንም በDCPS ኔትወርክ (network) ላይ የሚገኙ ወይም በDCPS ዲቫይሶች ላይ እንዲቀመጥ የተደረጉ ፋይሎችን፣ በማንኛውም-ጊዜ መፈተሽ እና ለማግኘት-እንዲችሉ የሚቀድላቸው ሊሆን ይችላል። በተወሰኑ-ሁኔታዎች ስር፣ በግል የሚዲያ አካውንታችሁን ወይም ዲቫይስን፣ ወይም ከግል ሚዲያ አካውንት ወይም ዲቫይሱ ውስጥ የሚገኘውን የመረጃ ስብስብን - የDCPS ሠራተኛ - ሊፈትሽ

ይችል-ይሆናል።

**ለተሰረቀ ወይም በድንገት ለተበላሸ ዲቫይሶች፣ ያሉት ፕሮቶኮሎች**

ዲቫይሳችሁ ከተሰረቀ ወይም የጉዳት-ብልሽት ገጥሞት ከነበረ፤ በተቻለ-ፍጥነት፣ ለአስተማሪ ወይም ለሠራተኛ-አባል ማሳወቅ አለባችሁ፤ ምክንያቱም DCPS ዲቫይሱ-ላይ ክትትል እንዲደረግበት - የተጠረጠረው ስርቆት በተፈጸመ በአምስት የቀን-መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ የፖሊስ ሪፖርትን ፋይል መደረግ አለበት። በስርቆት ለጠፋ ወይም በድንገት አደጋ-ከደረሰበት ዲቫይስ ጋር ተያያዥ-የሆኑ ክፍያዎችን ለመክፈት በኃላፊነት የምትጠየቁ አይሆንም። በዚህ ክስተት ውስጥ፣ ከDCPS ጋር ያላችሁ የትብብር-አጋርነት በጣም የሚመሰገን ነው።

**ተቀባይነት-የሌለው የቴክኖሎጂ አጠቃቀም - ምሳሌዎች**:

- ከDCPS ዲቫይሱ አጠገብ መብላት እና መጠጣት፤
- በDCPS ዲቫይሱ ላይ - መፃፍ፣ መሣል፣ ወይም ስቲከሮችን/stickersን መለጠፍ፤
- ከአስተማሪው ፈቃድ-ሳይሰጡ፤ ሙዚቃን፣ የቪዲዮ ፋይሎችን፣ ድህረ-ገጾችን፣ ሶፍትዌሮችን፣ አፖችን (apps)፣ የብራውሰር ተቀጥያዎችን (browser extensions)፣ ወይም ሚዲያን ጨምሮ - ማንኛውንም የፋይል ዓይነቶችን እንዲንቀሳቀሱ (run ማድረግ)፣ ዳውንሎች (download)፣ መጫን (install፤
- የጥበቃ-ማድረጊያ አቀማመጦች ( security settings)ን ወይም የኢንተርኔት ይዘት ማጣሪያዎች (internet content filters)ን ለመቀየር ሙከራ-ለማድረግ - መተግበሪያዎች (applications)ን ወይም 'plug-ins'ን መጠቀም፤
- የ'USB' ድራቮች/drivesን ማስገባት (ማለትም፤ ፍላሽ ድራቮች/flash drives)ን በአስተማሪው ተገቢ ሆኖ እንድታደርጉ ፈቃድ-ሳታገኙ ወደ ዲቫይሱ ማስገባት፤
- በጥላቻ-ላይ መሠረት ያደረጉ፣ አጸያፊ፣ ብልግና፣ ወዘተ... የመረጃ-ምንጮችን ላይ ፍለጋ-ማድረግ፣ ማስቀመጥ፣ ማሰራጨት ወይም እንዲታዩ-ማድረግ፤
- በማንኛውም ሕገ-ወጥ ወይም የወንደለኛነት ስራዎች ላይ ለመሳተፍ፣ የDCPS ኔትወርክን መጠቀም፤
- እነዚህ እንቅስቃሴዎች፤ ከትምህርት ቤት ስራ ጋር ካልተገናኙ እና አስተማሪ ወይም ሠራተኛ እንቅስቃሴውን እየተቆጣጠረ ካልሆነ በስተቀር፣ የኦንላይን ጨዋታዎች/online gamesን፣ ማህበራዊ ሚዲያን፣ የመልእክት መላላኪያ መተግበሪያዎች/messaging appsን ወይም የቡድን ውይይቶች/group chatsን መጠቀም፤
- በሌሎች ሰዎች ላይ፣ ማንጓጠጥ (Bullying)/የንዝነዛ-ትንኮሳ ማድረግ (harassing)፣ እንዲፈሩ-ማድረግ (threatening)፣ ወይም የዛቻ-ማስፈራሪያ (intimidating) ማድረግ፤
- የሌላ ሰውን - የመግቢያ ስም (login name) እና የሚስጥር መግቢያ ኮድ (password) መጠቀም፤ እና
- ያለፈቃዳቸው - የሌሎችን ምስሎች፣ ድምጽ (audio) ወይም የቪዲዮ ቅጂን፣ ማዘጋጀት ወይም መለጠፍ።

# የተማሪ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም የስምምነት እውቅና-መስጫ ቅፅ/Student Technology Responsible Use Agreement Acknowledgement Form

**ተማሪዎች: የDCPS 'ተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትዎርክ ተቀባይነት ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ (Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy)'ን እና 'የተማሪ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ኃላፊነት የሚሰማው የአጠቃቀም ስምምነት (Student Technology Use Responsible Use Agreement)'ን አንብአለሁ፣ ወይም ሌላ-ሰው ለእኔ አንብቦልኝ አስረድቶኛል።**

**ወላጆች/አሳዳጊዎች: የDCPS 'ተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትዎርክ ተቀባይነት ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ (Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy)'ን እና 'የተማሪ ቴክኖሎጂ ኃላፊነት የሚሰማው የአጠቃቀም ስምምነት (Student Technology Responsible Use Agreement)'ን፣ ከተማሪዬ ጋር ሆነን - የአነበቡት እና ውይይት-አድርገንበታል።**

1. የDCPS ዲቫይሶችን እና የDCPS ኔትዎርክን በስምምነቱ ዝርዝር ላይ በተጠቀሰው ደንቦች እና ተቀባይነት-ባለው የአጠቃቀም ፖሊሲ መሠረት፣ በኃላፊነት ለመጠቀም ተስማምቻለሁ። እነዚህን ደንቦች ካልተከተልኩ፤ በDCPS የስነ-ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎች ስር ሊያስከትል የሚችለውን-ቅጣት የምጋፈጥ መሆኔን እና፣ የDCPS ዲቫይሶችን እና የDCPS ኔትወርክን በማግኘት-ላይ ያለኝን ገደብ ውሱን-ሊያደርግብኝ እንደሚችል ተረድቻለሁ።

2. የDCPS ዲቫይስን ወይም የDCPS ኔትወርክን፤ ለማንጓጠጥ፣ ለማስፈራራት፣ ለዛቻ፣ ለማዋከብ፣ ወይም ሌላ ሰው ላይ ጥላቻን ለማንፀባረቅ ጥቅም-ላይ ሲውል ብመለከት ወይም ሌላ ሰው እንደሚጠቀምበት ከተገነዘብኩኝ፣ ይህን ለአስተማሪ ወይም የሠራተኛ-አባል፣ ሪፖርት እንደማደርግ ተገንዝቤአለሁ። ያቀረብኩት ሪፖርት በሚስጥር እንደሚያዝ፣ እና ሪፖርት በማድረጌ ሊደርስ የሚችለውን ማንኛውም የበቀል ጥቃትን፣ DCPS በትዕግስት እንደማያልፈው ተገንዝቤአለሁ።

3. ዲቫይስ ከተሰጠኝ፤ በDCPS ተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትዎርክ ተቀባይነት-ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ (DCPS Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy) መሠረት፣ ጥቅም-ላይ እንዲውል ብቻ - ለእኔ በተውሶ-እንደተሰጠ ተረድቻለሁ። በ2016 የተማሪዎች የዲጂታል የግል ደህንነት ጥበቃ ድንጋጌ (Protecting Students Digital Privacy Act of 2016) በመከተል፣ DCPS፣ የላፕቶፑን (the laptop) የመረጃ ስብስቦችን (data) የሚሰበስብ እና አጠቃቀሙን ይቆጣጠራል።

4. የDCPS ዲቫይሱ ከጠፋብኝ ወይም ሆን-ብዬ ወይም በቸልተኝነት ጉዳት ባደርስበት፤ ከDCPS ሚሰጠው - ተገቢውን የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወስድብኝ ይችላል። ለመጥፋቱ ወይም ለደረሰበት ጉዳት ምክንያቱ-ምን እንደሆነ ለመወሰን እና በኃላፊነት የዲቫይስ እንክብካቤ ልምዶችን ለማወቅ፤ ከDCPS ጋር መገናኘት ይጠበቅብኛል።

5. ዲቫይስ ከተሰጠኝ፤ ጥያቄው-በሚቀርበበት ጊዜ፣ ወደ ትምህርት ቤቱ የቴክኖሎጂ ግንኙነት-ሰራተኛ (Point of Contact) ወይም ወደ DCPS IT ቡድን (AssetAdmin@k12.dc.gov) መመለስ-እንዳለበት ተረድቻለሁ። በተጠየቀው-መሠረት ዲቫይሱን ካልመለስኩኝ፤ በርቀት/remotely ዲቫይሱ እንዳይሰራ-ሊደረግ እንደሚችል፣ እና ቤተሰቦቼ መክፈል-ያለባቸው ክፍያ ሊኖር ይችላል።

6. DCPS ከተመረቅሁ በኋላ፣ ወይም ምዝገባዬ ከተሰረዘ-በኋላ፤ የDCPS ቴክኖሎጂ ወይም ኔትወርክ የማግኘት መብት እንደሌለኝ ተረድቻለሁ።

# ሠራተኛ ቴክኖሎጂን በኃላፊነት የመጠቀም የስምምነት እውቅና-መስጫ ቅፅ (Staff Technology Responsible Use Agreement Acknowledgement Form)

**የDCPS 'ተማሪ እና ሠራተኛ በቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተገቢ-የሆነ የመጠቀሚያ ፖሊሲ/ Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy'ን፤ አንብቤዋለሁ።**

1. የDCPS ኔትወርክን ለመጠቀም እና ማንኛውም ለእኔ ከDCPS ለተሰጠኝ ዲቫይስ - ተቀባይነት-ባለይው የአጠቃቀም ፖሊሲ (Acceptable Use Policy) ስር በተዘረዘሩት ደንቦች መሠረት በኃላፊነት ለመጠቀም ተስማምቻችልሁ። እነዚህን ደንቦች ካልተከተልኩኝ፤ በDCPS የስነ-ስርዓት ደንቦች እና ፖሊሲዎች ስር፣ ሊያስከትል የሚችለውን-ቅጣት የምጋፈጥ መሆኔን ተረድቻለሁ።

2. በDCPS - ላፕቶፕ (laptop) ከተሰጠኝ፤ ላፕቶፑ (laptop) በDCPS ባለቤትነት-ስር መሆኑን እውቅና-እሰጣለሁ። ይህ ላፕቶፕ (laptop)፣ ከDCPS የተማሪ እና ሠራተኛ ቴክኖሎጂ እና ኔትወርክ ተቀባይነት-ያለው የአጠቃቀም ፖሊሲ (Student and Staff Technology and Network Acceptable Use Policy) ጋር መሠረት አድርጎ፣ ለስራ- ዓላማዎች ብቻ ጥቅም-ላይ እንዲውል በDCPS ለእኔ በተውሰ-የተሰጠ ነው።

3. በDCPS - ላፕቶፕ (laptop) ከተሰጠኝ፤ በእኔ ቸልተኝነት ወይም ሆን-ብዬ ባደረኩት እርምጃዎች ከሚደርሱ ብልሽቶች ጋር ተያያዥ-የሆኑ ማንኛውንም የማስጠገኛ ክፍያዎችን ለመክፈል ኃላፊነት አለብኝ።

4. በDCPS - ላፕቶፕ (laptop) ከተሰጠኝ፤ ድርጅቱን-ለቅቄ የምሄድ ከሆነ ወይም በምጠየቅ-ጊዜ -ላፕቶፑ ( the laptop) ወደ 'DCPS IT' ቡድን (AssetAdmin@k12.dc.gov) መመለስ-አለብኝ። በDCPS በምጠየቅ ጊዜ - ይህን ዲቫይስ መመለስ አለመቻል፣ ክፍያውን እንድከፍል ሊያደርገኝ ይችላል።